## ማውጫ

| | | | ገጽ |
|---|---|---|---|
| የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ | | | ፩ |

### ምዕራፍ አንድ
### ስለጋብቻ አፈፃፀም

| | | | |
|---|---|---|---|
| ክፍል | ፩· | ጠቅላላ | ፫ |
| ክፍል | ፪· | ጋብቻ ለመፈፀም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች | ፬ |
| ክፍል | ፫· | ጋብቻ እንዳይፈጸም ስለመቃወም | ፯ |
| ክፍል | ፬· | በክብር መዝገብ ሹም ፊት ስለሚፈጸም ጋብቻ | ፱ |
| ክፍል | ፭· | ሌሎች የጋብቻ አፈጻጸም ሥርዓቶች | ፲ |
| ክፍል | ፮· | ስለጋብቻ ምዝገባ | ፲ |

### ምዕራፍ ሁለት

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | የጋብቻ ሁኔታዎች አለመሟላት የሚያስከትለው ውጤት | ፲፩ |

### ምዕራፍ ሦስት

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | የጋብቻ ውጤት | ፲፬ |
| ክፍል | ፩· | ጠቅላላ | ፲፬ |
| ክፍል | ፪· | ጋብቻ በተጋቢዎች ግላዊ ግንኙነት ላይ ስለሚኖረው ውጤት | ፲፯ |
| ክፍል | ፫· | ጋብቻ በንብረት በኩል ስለሚኖረው ውጤት | ፲፯ |

### ምዕራፍ አራት

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ስለጋብቻ መፍረስ | ፳፫ |
| ክፍል | ፩· | በስምምነት ስለመፋታት | ፳፬ |

ክፍል ፪· ጥያቄ በመቅረቡ ምክንያት ስለሚወሰን ፍቺ ........ ፳፫

## ምዕራፍ አምስት
የባልና ሚስትን ሀብት ስለማጣራት ........ ፳፰

## ምዕራፍ ስድስት
ጋብቻ ለመፈፀሙ ስለሚቀርብ ማስረጃ ........ ፴፩

## ምዕራፍ ሰባት
ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ ስለመኖር ........ ፴፪

## ምዕራፍ ስምንት
በጋብቻና ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ በመኖር የሚነሱ ክርክሮችን ስለመወሰን ........ ፴፫

ክፍል ፩· ጠቅላላ ........ ፴፫

ክፍል ፪· ስለ ፍርድ ቤት ሥልጣን ........ ፴፯

ክፍል ፫· ስለ ዕርቅ ........ ፴፰

## ምዕራፍ ዘጠኝ
ስለመወለድ ........ ፵

ክፍል ፩· አባትነትና እናትነትን ስለማወቅ ........ ፵

ንዑስ ክፍል ፩· አጠቃላይ ድንጋጌዎች ........ ፵

ንዑስ ክፍል ፪· አባትነት በሕግ ግምት የሚታወቅ ስለመሆኑ ........ ፵

ንዑስ ክፍል ፫· ልጅነትን ስለመቀበል ........ ፵፩

ንዑስ ክፍል ፬· በፍርድ ቤት ውሳኔ አባትነት እንዲታወቅ ስለማድረግ ........ ፵፬

ክፍል ፪· አባትነትን በመወሰን ላይ ስለሚኖረው የሕግ ግጭት ........ ፺፭

ክፍል ፫· ስለልጅነት ማስረጃ ........ ፺፯

ክፍል ፬· በተወላጅነት ላይ ስለሚነሳ ክርክርና ስለመካድ ........ ፺፱

ንዑስ ክፍል ፩· በተወላጅነት ላይ ስለሚነሳ ክርክር ........ ፺፱

ንዑስ ክፍል ፪· ስለመካድ ........ ፺፱


## ምዕራፍ አሥር


ስለጉዲፈቻ ........ ፻፪


## ምዕራፍ አሥራ አንድ


ቀለብ የመስጠት ግዴታ ........ ፻፰


## ምዕራፍ አሥራ ሁለት


አካለመጠን ስላልደረሱ ሰዎች ........ ፻፲፪

ክፍል ፩· ጠቅላላ ድንጋጌዎች ........ ፻፲፪

ክፍል ፪· አካለመጠን ያልደረሰን ልጅ ስለሚጠብቁ ተቋሞች ........ ፻፲፫

ክፍል ፫· የአሳዳሪውና የሞግዚቱ ሥልጣን ........ ፻፳፬

ንዑስ ክፍል ፩· አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ አስተዳ ደግና ጥበቃ ........ ፻፳፬

ንዑስ ክፍል ፪· አካለመጠን ያልደረሰን ልጅ ንብረት ስለማስተዳደር ........ ፻፳፰

ክፍል ፬· አካለመጠን ያልደረሰን ልጅ ለመጠበቅ የተመለከቱትን ደንቦች መጣስ ስለሚያ ስከትለው ውጤት ........ ፻፴፯

ንዑስ ክፍል ፩· አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ሥራዎች ........ ፻፴፯

ንዑስ ክፍል ፪· የሞግዚቱ ሕጋዊ ድርጊቶች ........ ፻፴፰

ንዑስ ክፍል ፫· በኃላፊነት ሊያስጠይቁ ስለሚችሉ ድርጊቶች ፻፴፱

ክፍል ፯· አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ችሎታ ማጣት ስለመቅረቱ ....... ፺

ንዑስ ክፍል ፩· ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ስለመውጣት ....... ፺፩

ንዑስ ክፍል ፪· የሞግዚትነት ሥራ ሂሳቦችን ስለማስ ታወቅ ....... ፺፩

ምዕራፍ አስራ ሦስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ....... ፺፫

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

፮ኛ ዓመት
ልዩ ዕትም ቁጥር ፩

አዲስ አበባ
ሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ጠባቂነት የወጣ

# የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ልዩ ዕትም ቁጥር ፩/፲፱፻፺፪ ዓ.ም.
በአዋጅ ቁጥር ፪፻፲፫/፲፱፻፺፪ ዓ.ም የወጣ
የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ

BACK

# አዋጅ ቁጥር ፪፻፲፫/፲፱፻፺፪ ዓ.ም
# የ፲፱፻፺፪ ዓ.ም የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ

## <u>አዋጅ</u>

## <u>መግቢያ</u>

ቤተሰብ የሕብረተሰብ የተፈጥሮ መነሻ በመሆኑና በሕብረተሰብና በመንግሥት ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ መሆኑን በማመን ፤ የመንግሥት ጥበቃ የሚገለጽበት አንዱ መንገድም የቤተሰብ ግንኙነትን በሕግ መደንገግና መግዛት መሆኑን በመገንዘብ ፤

በሥራ ላይ ያለው የኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ አሁን ካለንበት የሕብረተሰብ የእድገት ደረጃ፡ በዋነኛነትም ከሕገመንግሥቱ ጋር እንዲ ጣጣም ማድረግ በማስፈለጉና ፤ በተለይም ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ ላይ ብቻ መመሥረት ያለበት መሆኑንና በጋብቻ አፈፃፀም ፣ በጋብቻ ዘመንና በፍቺ ጊዜ የተጋቢዎችን የእኩልነት መብት የሚያስ ጠብቅ ሕግ ማውጣት አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ ፤

የልጆችን ደህንነት ፣ አስተዳደግና አጠባበቅን አስመልክቶ ሕገ መንግሥቱና ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በሚጠ ይቁት መሠረት የሕፃናትን ደህንነት ቀደምትነት በሚሰጥ መልኩ ሕጉን አሻሽሎ መቅረጽ በማስፈለጉ፡

በቤተሰብ ውስጥ የሚነሱ ክርክሮችን ፍትሐዊ በሆነና በተቀላጠፈ ሁኔታ ብቃት ባለው አካል እንዲዳኙ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፤

ይህን እውን ለማድረግም ተጠሪነታቸው በቀጥታ ለፌዴራሉ መንግሥት በሆኑ መስተዳድሮች ተፈፃሚነት የሚኖረው የቤተሰብ ሕግ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መውጣት ያለበት በመሆኑ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) መሠረት ከዚህ የሚከተለው ታውጇል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር ፪፻፲፫/፲፱፻፺፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

BACK



## ፫· ሕጉ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ የ፲፱፻፺፪ ዓ·ም የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ፡ በተለይ በቁጥር ፩/፲፱፻፺፪ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ የታተመው፡ ከሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ·ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ·ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

## ምዕራፍ አንድ
## ስለ ጋብቻ አፈጻጸም
## ክፍል ፩
## ጠቅላላ

### አንቀጽ ፩ ልዩ ልዩ የጋብቻ አፈጻጸም ሥርዓቶች

፩· ጋብቻ በአንድ የክብር መዝገብ ሹም ፊት ሊፈጸም ይችላል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው ቢኖርም ፣ ጋብቻ በተጋቢዎቹ ሃይማኖት ወይም ባህል መሠረት ሊፈፀም ይችላል።

### አንቀጽ ፪ በክብር መዝገብ ሹም ፊት የሚፈፀም ጋብቻ

ጋብቻ በክብር መዝገብ ሹም ፊት ተፈፀመ የሚባለው አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት ጋብቻ ለመፈፀም ተስማምተው በክብር መዝገብ ሹም ፊት በመቅረብ ፈቃዳቸውን ሲገልጹና የክብር መዝገብ ሹሙም ይህንኑ ፈቃዳቸውን ሲቀበል ነው።

### አንቀጽ ፫ በሃይማኖት ሥርዓት መሠረት የሚፈፀም ጋብቻ

ጋብቻ በሃይማኖት ሥርዓት መሠረት ተፈጸመ የሚባለው ፣ አንድ ወንድና አንዲት ሴት በሃይማኖታቸው ወይም ከሁለቱ በአንዳቸው ሃይማኖት መሠረት የሚፀና ጋብቻ ለማቋቋም የሚያስፈልገውን ሥርዓት ሲፈጽሙ ነው።

### አንቀጽ ፬ በባህል ሥርዓት መሠረት የሚፈፀም ጋብቻ

ጋብቻ በባህል ሥርዓት መሠረት ተፈፀመ የሚባለው ፣ አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት በሚኖሩበት አካባቢ ባህል ወይም በሁለቱ ተጋቢዎች ወይም ከሁለቱ ተጋቢዎች በአንዳቸው ባህል መሠረት የሚፀና ጋብቻ ለማቋቋም የሚያስፈልገውን ሥርዓት ሲፈጽሙ ነው።

**አንቀጽ ፫ ከኢትዮጵያ ውጭ ስለሚፈፀም ጋብቻ**

በተፈፀመበት አገር የጋብቻ አፈፃፀም ሕግ መሠረት ከኢትዮጵያ ውጭ የተፈፀመ ጋብቻ የሕዝብን ሞራል እስካልተቃረነ ድረስ በዚህ ሕግ ተቀባይነት ይኖረዋል።

## ክፍል ፪
## ጋብቻ ለመፈፀም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

**አንቀጽ ፮ ፈቃድ**

የሚፀና ጋብቻ ተፈፀመ የሚባለው ተጋቢዎቹ ለመጋባት ነፃና ሙሉ ፈቃዳቸውን ሲሰጡ ብቻ ነው።

**አንቀጽ ፯ ዕድሜ**

፩· ወንዱም ሆነ ሴቷ አሥራ ስምንት ዓመት ሳይሞላቸው ጋብቻ መፈፀም አይችሉም ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ፣ ከባድ ምክንያት ሲያጋጥም ተጋቢዎቹ ወይም ከተጋቢዎቹ የአን ዳቸው ወላጆች ወይም አሳዳሪ በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት የፍትሕ ሚኒስትሩ ከመደበኛው የጋብቻ ዕድሜ ከሁለት ዓመት ያልበለጠ ጊዜ በመቀነስ እንዲጋቡ ሊፈቅድ ይችላል።

**አንቀጽ ፰ የሥጋ ዝምድና**

፩· በቀጥታ የሥጋ ዘመዳሞች (በወላጆችና በተወላጆች) መካከል ጋብቻ መፈፀም ክልክል ነው።

፪· ወደ ጐን በሚቆጠር የሥጋ ዝምድና ፣ አንድ ወንድ ከእህቱ ወይም ከአክስቱ፤ እንዲሁም አንዲት ሴት ከወንድሟ ወይም ከአጎቷ ጋር ጋብቻ መፈፀም የተከለከለ ነው።

BACK



## አንቀጽ ፱ የጋብቻ ዝምድና

፩· በቀጥታ የጋብቻ ዘመዳሞች መካከል ጋብቻ መፈጸም ክልክል ነው።

፪· ወደ ጐን በሚቆጠር የጋብቻ ዝምድና ፣ ባል ከሚስቱ እህት ወይም ሚስት ከባሏ ወንድም ጋር ጋብቻ መፈፀም ክልክል ነው።

## አንቀጽ ፲ በሕግ ያልተረጋገጠ ልጅነት

የአንድ ሰው ተወላጅነት በሕግ መሠረት ያልተረጋገጠ ቢሆንም እንኳን በማኅበረሰቡ ዘንድ በተወላጅነት የሚታወቅ ከሆነ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፰ እና ፱ እንደተመለከተው ጋብቻን ለማስከልከል በቂ ነው።

## አንቀጽ ፲፩ በጋብቻ ላይ ጋብቻ

ማንኛውም ሰው አስቀድሞ በጋብቻ የተሳሰረ ከሆነ ፣ ይኸው ጋብቻው ፀንቶ ባለበት ጊዜ ሌላ ጋብቻ መፈፀም አይችልም።

## አንቀጽ ፲፪ ጋብቻን በእንደራሴ መፈጸም የማይቻል ስለመሆኑ

፩· ጋብቻ ሲፈፀም ሁለቱም ተጋቢዎች ጋብቻው በሚፈፀምበት ጊዜ በግንባር ተገኝተው ፈቃዳቸውን መስጠት አለባቸው ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ፣ ከባድ ምክንያት መኖሩን እና በእንደራሴ አማካይነት ጋብቻውን ለመፈፀም የሚፈልገው ተጋቢ ፈቃዱን በማያሻማ ሁኔታ የገለፀ መሆኑን የፍትሕ ሚኒስትሩ ሲያረጋግጥ ጋብቻው በእንደራሴ ሊፈፀም ይችላል።

## አንቀጽ ፲፫ መሠረታዊ ስህተት

፩· በስህተት በተገኘ ፈቃድ ምክንያት የተፈፀመ ጋብቻ አይፀናም።

፪· በስህተት ምክንያት ፈቃድ ተጓደለ የሚባለው ስህተቱ መሠረታዊ ሆኖ ሲገኝ ነው።

BACK



፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተገለፀው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ፡ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ መሠረታዊ ስህተት እንዳለ ይቆጠራል፣

ሀ) በሚያገባው ሰው ማንነት ላይ በመሳሳቱ ምክንያት አገባ ዋለሁ ብሎ ያላሰበውን ሰው ያገባ ሲሆን፤

ለ) የሚያገባው ሰው ሊድን የማይችል ከባድ በሽታ ወይም ለተወላጆች ሊተላለፍ የሚችል ነዋሪ በሽታ ያለበት መሆኑን ሳያውቅ ያገባው ሲሆን፣

ሐ) ሌላው ተጋቢ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈፀም የማይችል መሆኑን ባለማወቁ ምክንያት ያገባው ሲሆን፤

መ) ሌላው ተጋቢ ከተመሳሳይ ጾታ ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት የመፈጸም ልማድ ያለው መሆኑን ባለማወቅ ምክንያት ያገባው ሲሆን።

## አንቀጽ ፲፬ በኃይል ሥራ የተገኘ ፈቃድ

፩· በኃይል ሥራ በተገኘ ፈቃድ ምክንያት የተፈፀመ ጋብቻ አይፀናም።

፪· ፈቃድ በኃይል የተገኘ ነው የሚባለው ፡ ፈቃዱን የሰጠው ተጋቢ ራሱን ወይም ከወላጆቹ ወይም ከተወላጆቹ አንዱን ወይም ሌላ ለእርሱ የቅርብ ዘመድ የሆነን ሰው ሊፈፀምበት ከተቃረበ ከባድ አደጋ ለማዳን ሲል ፈቃዱን የሰጠ ሲሆን ነው።

## አንቀጽ ፲፭ በፍርድ ስለተከለከለ ሰው ጋብቻ

፩· በፍርድ የተከለከለ ማንኛውም ሰው ፡ ፍርድ ቤት ካልፈቀደለት በስተቀር ጋብቻ መፈፀም አይችልም።

፪· ስለዚህ ጉዳይ ለፍርድ ቤት የሚቀርበውን ጥያቄ የተከለከለው ሰው ራሱ ወይም አሳዳሪው ሊያቀርበው ይችላል።

BACK



## አንቀጽ ፲፯ በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነ ጊዜ

፩· አንዲት ሴት አስቀድሞ የነበራት ጋብቻ ከቀረ በኋላ ፡ አንድ መቶ ሰማንያ ቀን ካላለፈ በስተቀር እንደገና ከሌላ ሰው ጋር ጋብቻ መፈጸም አትችልም።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ፡ ሴቲቱ አስቀድሞ የነበራት ጋብቻ ከቀረ በኋላ አንድ መቶ ሰማንያ ቀን ሳይሞላ፡

ሀ) የወለደች እንደሆነ ፡ ወይም

ለ) ጋብቻ የምትፈጽመው ከቀድሞ ባሏ ጋር የሆነ እንደሆነ ፡ ወይም

ሐ) እርጉዝ አለመሆኗ በሕክምና የተረጋገጠ እንደሆነ ፡ ወይም

መ) በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነውን ጊዜ እንዳትጠብቅ ፍርድ ቤት የወሰነ እንደሆነ፡

በብቸኝነት ለመኖር ስለተወሰነው ጊዜ የተደነገገው ተፈፃሚ አይሆንም።

### ክፍል ፫

### ጋብቻ እንዳይፈጸም ስለመቃወም

## አንቀጽ ፲፰ ስለመቃወም

ጋብቻ ለመፈፀም አስፈላጊ የሆነ ሁኔታ አልተሟላም በማለት ሊፈፀም የታሰበ ጋብቻ እንዳይፈፀም ተቃውሞ ማቅረብ ይቻላል።

## አንቀጽ ፲፱ መቃወም ስለሚችሉ ወገኖች

ጋብቻ እንዳይፈፀም መቃወም የሚችሉት ወገኖች የሚከተሉት ብቻ ናቸው፡

ሀ) በዕድሜ ምክንያት ሲሆን ወላጆች ፡ ዐቃቤ ሕግ ወይም ሌላ ማንኛውም ያገባኛል የሚል ሰው ፤

ለ) በሥጋ ወይም በጋብቻ ዝምድና ምክንያት ሲሆን ፡ የተጋቢዎቹ ወይም የአንደኛው ተጋቢ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ፡ ፲፰ ዓመት የሞላቸው ወንድሞች ወይም እህቶች ወይም ዐቃቤ ሕግ፡

ሐ) በጋብቻ ላይ ጋብቻ ሊፈፀም ሲሆን ሌላ ጋብቻ ከሚፈጽመው ሰው ጋር የቀደመ ጋብቻ አለኝ የሚለው ተጋቢ ወይም ዐቃቤ ሕግ ፡

መ) በፍርድ በመከልከል ምክንያት ሲሆን አሳዳሪው ወይም ዐቃቤ ሕግ።

## አንቀጽ ፲፱ መቃወሚያ ስለሚቀርብበት ሥርዓትና ጊዜ

፩· ጋብቻ እንዳይፈፀም የሚቀርበው መቃወሚያ በጽሑፍ ሆኖ እ፳ግ ቢዘገይ ጋብቻው ከሚፈፀምበት ከ፲፭ ቀን በፊት ለጋብቻ አስፈፃሚው ባለሥልጣን መቅረብ አለበት ።

፪· ጋብቻ አስፈፃሚው ባለሥልጣን በመቃወሚያው ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት የተጋቢዎቹን አስተያየት መቀበል ይኖር በታል።

## አንቀጽ ፳ በመቃወሚያ ላይ ስለሚሰጠው ውሳኔ

፩· ጋብቻ የሚያስፈጽመው ባለሥልጣን በሚቀርብለት መቃወሚያ ላይ በአምስት ቀን ጊዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት።

፪· ጋብቻ አስፈፃሚው ባለሥልጣን መቃወሚያውን ባለመቀበል ጋብቻው እንዲፈፀም የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

፫· ጋብቻ አስፈፃሚው ባለሥልጣን መቃሠሚያውን የተቀበለው እንደሆነ ጋብቻው እንዳይፈጸም ማድረግ አለበት ።

፬· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከተው ውሳኔ የተሰጠ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ለውሳኔው ምክንያት ያደረገውን ጉዳይ ተጋቢዎቹ ወዲያውኑ እንዲያውቁት ያደርጋል።

## አንቀጽ ፳፩ ስለይግባኝ

፩· በዚህ ሕግ አንቀጽ ፳ ንዑስ አንቀጽ (፫) በተመለከተው ሁኔታ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ተጋቢዎቹ ወይም ከተጋቢዎቹ አንዱ ለፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

BACK



፪· ይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤት የጋብቻ አስፈፃሚውን ባለሥልጣን ውሳኔ የሻረው እንደሆነ ባለሥልጣኑ ጋብቻውን ያስፈጽማል።

## ክፍል ፬
## በክብር መዝገብ ሹም ፊት ስለሚፈፀም ጋብቻ

### አንቀጽ ፳፪ ሥልጣን ያለው የክብር መዝገብ ሹም

ጋብቻ ከተጋቢዎቹ አንዱ ወይም ከተጋቢዎቹ ወላጆች ወይም የቅርብ ዘመዶች አንዱ ጋብቻው ከሚፈጸምበት ጊዜ በፊት ቢያንስ ለስድስት ወራት ያህል ሳያቋርጥ በሚኖርበት ቦታ በሚገኘው የክብር መዝገብ ሹም ፊት ይፈጸማል።

### አንቀጽ ፳፫ ጋብቻ ለመፈፀም ጥያቄ ስለማቅረብ እና ስለሚቀርብበት ጊዜ

ተጋቢዎች ጋብቻ ለመፈፀም ማሰባቸውን እጅግ ቢዘገይ ጋብቻቸውን ለመፈፀም ከወሰኑበት ቀን ከአንድ ወር በፊት ለክብር መዝገብ ሹሙ ማስታወቅ አለባቸው።

### አንቀጽ ፳፬ ጋብቻ የሚፈፀምበትን ቀን ስለመወሰንና ስለማስታወቅ

የክብር መዝገብ ሹሙ ጥያቄው እንደቀረበለት ከተጋቢዎቹ ጋር በመነጋገር ከወሰነ በኋላ፥ ጋብቻው የሚፈፀምበትን ቀን በመግለጽ አመቺ በሆነው መንገድ ማስታወቂያ ያወጣል።

### አንቀጽ ፳፭ የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት እና ጋብቻው መፈፀሙን ስለማስታወቅ

፩· ጋብቻው ሁለቱ ተጋቢዎች እና ከእያንዳንዱ ተጋቢ በኩል ሁለት ሁለት ምስክሮች በተገኙበት በግልጽ ይፈፀማል።

፪· ተጋቢዎችና ምስክሮቹ ጋብቻ ለመፈፀም አስፈላጊ የሆኑት ሁኔታዎች አለመጣሳቸውን በቃለ መሐላ ያረጋግጣሉ።

፫· ተጋቢዎችና ምስክሮቹ የመሐላ ቃል ከመስጠታቸው በፊት የሚሰጡት ቃል ስለሚያስከትለው ኃላፊነት የክብር መዝገብ

BACK



ሹሙ በግልጽ ማስረዳት አለበት።

፬· ሁለቱም ተጋቢዎች ጋብቻ ለመፈፀም መፍቀዳቸውን ለክብር መዝገብ ሹሙ በግልጽ ያረጋግጣሉ።

፭· ሁለቱም ተጋቢዎችና ምስክሮቻቸው በክብር መዝገብ ላይ መፈረም አለባቸው።

፮· ከዚህ በላይ የተገለጹት ሥርዓቶች የተፈፀሙ መሆናቸውን ሲያረጋግጥ የክብር መዝገብ ሹሙ ተጋቢዎቹ በሕጋዊ ጋብቻ የተሳሰሩ መሆናቸውን አስታውቆ ለተጋቢዎቹ የጋብቻ የምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል።

## ክፍል ፫
## ሌሎች የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓቶች

### አንቀጽ ፳፮ በሃይማኖት ሥርዓት የሚፈፀም ጋብቻ

፩· በሃይማኖት ሥርዓት መሠረት ጋብቻ ሊፈፀም የሚችልበትና የአፈፃፀሙ ሥርዓት እንደየሃይማኖቱ ይወሰናል።

፪· በዚህ ሕግ ለማንኛውም የጋብቻ አፈፃፀም መሟላት አለባቸው የተባሉት ሁኔታዎች በሃይማኖት ሥርዓት መሠረት ለሚፈፀም ጋብቻም መሟላት አለባቸው።

### አንቀጽ ፳፯ በባህል ሥርዓት ስለሚፈፀም ጋብቻ

፩· በባሕል ሥርዓት መሠረት ጋብቻ ሊፈፀም የሚችልበትና የአፈፃፀሙ ሥርዓት በአካባቢው ባሕል ይወሰናል።

፪· በዚህ ሕግ ለጋብቻ አፈፃፀም መሟላት አለባቸው የተባሉት ሁኔታዎች በባህል ሥርዓት መሠረት ለሚፈፀም ጋብቻም መሟላት አለባቸው።

## ክፍል ፬
## ስለጋብቻ ምዝገባ

### አንቀጽ ፳፰ ጋብቻን ስለማስመዝገብ

፩· ጋብቻው የተፈፀመው በማንኛውም የጋብቻ አፈፃፀም

BACK



ሥርዓት ቢሆንም ፡ አግባብ ባለው የክብር መዝገብ ሹም መመዝገብ አለበት።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ምዝገባውን ያከናወነ የክብር መዝገብ ሹም ለተጋቢዎቹ የጋብቻ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

፫· ማንኛውም ጋብቻ ከተፈፀመበት ቀን ጀምሮ ውጤት ይኖረዋል።

## አንቀጽ ፳፱ የጋብቻ መዝገብ ስለማደራጀት

፩· በዚህ ሕግ አንቀጽ ፳፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ተጋቢዎች ጋብቻውን ያላስመዘገቡ ቢሆንም እንኳን ፣ የክብር መዝገብ ሹሙ ጋብቻ መፈፀሙን ያወቀ እንደሆነ የጋብቻ መዝገብ በሥልጣኑ ያደራጃል።

፪· ይህ በሚሆንበት ጊዜ የክብር መዝገብ ሹሙ ተጋቢዎቹና እንደ ነገሩ ሁኔታ ምስክሮች ቀርበው በጋብቻው መዝገብ ላይ እንዲፈርሙ ያደርጋል።

## አንቀጽ ፴ የጋብቻ መዝገብ ይዘት

የጋብቻ መዝገብ የሚያመለክተው፡

ሀ) የተጋቢዎችን ሙሉ ስም ፡ የተወለዱበትን ቀንና ቦታ ፡ የመኖሪያ አድራሻቸውን፡

ለ) የምስክሮችን ሙሉ ስም ፡ የተወለዱበትን ቀንና ቦታ ፡ የመኖሪያ አድራሻቸውን፡

ሐ) ጋብቻው የተፈፀመበትን ሥርዓት ፡ ቀንና ቦታ እንዲሁም የተመዘገበበትን ቀን ይሆናል።

## ምዕራፍ ሁለት
## የጋብቻ ሁኔታዎች አለመሟላት የሚያስከትለው ውጤት

## አንቀጽ ፴፩ የዕድሜ ሁኔታ

፩· በዚህ ሕግ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደተ ጠበቀ ሆኖ ፡ ዕድሜአቸው ከአሥራ ስምንት ዓመት በታች በሆኑ

BACK



ሰዎች መካከል የተፈፀመ ጋብቻ በማንኛውም ባለጉዳይ ወይም በዐቃቤ ሕግ ጥያቄ እንዲፈርስ ይደረጋል።

፪· ሕጉ የሚጠይቀው የጋብቻ ዕድሜ ከተሟላ በኋላ ጋብቻው እንዲፈርስ ጥያቄ ማቅረብም ሆነ መወሰን አይቻልም ።

አንቀጽ ፴፪ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና

በሥጋ ወይም በጋብቻ ዝምድና ምክንያት ጋብቻ እንዳይፈጸም የተደነገገውን ክልከላ በመተላለፍ የተፈጸመ ጋብቻ በማንኛውም ባለጉዳይ ወይም በዐቃቤ ሕግ ጥያቄ እንዲፈርስ ይደረጋል።

አንቀጽ ፴፫ በጋብቻ ላይ ጋብቻ

፩· በጋብቻ ላይ ሌላ ጋብቻ ተፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ በመጀመሪያው ወይም በሁለተኛው ተጋቢ ወይም በዐቃቤ ሕግ ጥያቄ የኋለኛው ጋብቻ እንዲፈርስ ይደረጋል።

፪· ሆኖም የመጀመሪያው ተጋቢ የሞተ እንደሆነ የኋለኛው ጋብቻ እንዲፈርስ መጠየቅ አይቻልም።

አንቀጽ ፴፬ በፍርድ ክልከላ ምክንያት ጋብቻን ስለማፍረስ

፩· በፍርድ የተከለከለ ሰው ፍርድ ቤት ሳይፈቅድ ጋብቻ ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ ፡ የተከለከለው ሰው ራሱ ወይም አሳዳሪው ጋብቻው እንዲፈርስ ጥያቄውን ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል።

፪· የተከለከለው ሰው ጋብቻው እንዲፈርስ የሚያቀርበው ጥያቄ ክልከላው ከቀረበት ቀን ጀምሮ ስድስት ወር ካለፈ በኋላ ሊቀርብ አይችልም።

፫· ጋብቻው እንዲፈርስ በአሳዳሪው የሚቀርበው ጥያቄ ጋብቻው መፈፀሙን ከአወቀበት ቀን ጀምሮ ከስድስት ወር በኋላ ወይም በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ክልከላው ከቀረ በኋላ ሊቀርብ አይችልም።

አንቀጽ ፴፭ በኃይል ተግባር የተፈፀመ ጋብቻን ስለማፍረስ

፩· ማንኛውም ሰው ተገዶ ጋብቻ የፈጸመ እንደሆነ ፡ ጋብቻው እንዲፈርስ ጥያቄውን ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል።

፪· ስለዚህ ጉዳይ የሚቀርበው ጥያቄ የኃይል ሥራው ከቀረበት ከስድስት ወር በኋላ እና በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ጋብቻው ከተፈፀመ ከሁለት ዓመት በኋላ ሊቀርብ አይችልም።

## አንቀጽ ፴፯ በስህተት ምክንያት የተፈጸመ ጋብቻን ስለማፍረስ

፩· ማንኛውም ሰው ከመሠረታዊ ስህተት በመነሳት ጋብቻ የፈፀመ እንደሆነ ጋብቻው እንዲፈርስ ጥያቄውን ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል።

፪· ስለዚህ ጉዳይ የሚቀርበው ጥያቄ መሳሳቱን ከአወቀበት ቀን ጀምሮ ከስድስት ወር በኋላ እና በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ጋብቻው ከተፈፀመ ከሁለት ዓመት በኋላ ሊቀርብ አይችልም።

## አንቀጽ ፴፯ በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነውን ጊዜ ስላለመጠበቅ

በዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነው ጊዜ አልተከበረም በሚል ምክንያት ብቻ ጋብቻ እንዲፈርስ ጥያቄ ሊቀርብ አይችልም።

## አንቀጽ ፴፰ የክብር መዝገብ ሹም ሥልጣን የሌለው ስለመሆኑ

ጋብቻውን ያስፈጸመው የክብር መዝገብ ሹም በአንቀጽ ፳፪ መሠረት ሥልጣን አልነበረውም በሚለት ብቻ ጋብቻው እንዲፈርስ ለመወሰን አይቻልም።

## አንቀጽ ፴፱ የሥነ ሥርዓት አለመጠበቅ

በዚህ ሕግ አንቀጽ ፳፫ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፯) የተመለከቱት ሥርዓቶች አልተጠበቁም በማለት ብቻ ጋብቻ እንዲፈርስ ሊወሰን አይችልም።

## ምዕራፍ ሦስት
## የጋብቻ ውጤት
## ክፍል ፩
## ጠቅላላ

**አንቀጽ ፵ ሁሉም የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓቶች ተመሳሳይ ውጤት ያላቸው ስለመሆኑ**

፩· በማናቸውም ዓይነት የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት መሠረት የተፈፀመ ጋብቻ ፡ ተመሳሳይ ሕጋዊ ውጤት ይኖረዋል።

፪· በዚህ ረገድ ጋብቻ በክብር መዝገብ ሹም ፊት ወይም በሃይማኖት ወይም በባህል በታዘዙት ሥርዓቶች መሠረት የተፈፀመም ቢሆን ልዩነት አይደረግበትም።

**አንቀጽ ፵፩ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት መፈፀም**

የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት በዕውነት መፈፀሙ ወይም ተፈጽሟል ተብሎ መገመቱ ፡ ጋብቻው ለሚያስከትለው ውጤት አስፈላጊ አይደለም።

**አንቀጽ ፵፪ (፩) የጋብቻ ውል**

፩· ተጋቢዎቹ ጋብቻቸው ንብረታቸውን በተመለከተ ስለሚያስከትለው ውጤት ጋብቻቸውን ከመፈፀማቸው በፊት ወይም እጅግ ቢዘገይ ጋብቻቸው በሚፈፀምበት ዕለት በውል መወሰን ይችላሉ።

፪· እንዲሁም ግላዊ ግንኙነታቸውን በሚመለከት የሚኖሯቸውን መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ውል መወሰን ይችላሉ።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት ተጋቢዎቹ የሚያደርጓቸው ውሎች አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌዎችን የሚቃረኑ ሊሆኑ አይችሉም።

**አንቀጽ ፵፫ (፪) የተጋቢዎቹ ችሎታ ማጣት**

፩· በፍርድ የተከለከለ ሰው ፡ የሚያደርገውን የጋብቻ ውል እርሱ

BACK



ራሱ ካልፈፀመውና ፍርድ ቤት ካላፀደቀው በስተቀር ውጤት አይኖረውም።

፪. በሕግ የተከለከለ ሰው ፣ የጋብቻ ውል መዋዋልን በተመለከተ ችሎታ እንዳለው ይቆጠራል ።

## አንቀጽ ፵፬ (፫) የውሉ ፎርም

የጋብቻ ውል በጽሑፍ ካልተደረገና አራት ምስክሮች ፣ ሁለት በባል ወገን፡ ሁለት በሚስት ወገን ፣ የፈረሙበት ካልሆነ በስተቀር ውጤት አይኖረውም።

## አንቀጽ ፵፭ (፬) የውሉ ሰነድ ስለሚቀመጥበት ቦታ

፩. የጋብቻ ውሉ አንድ ቅጅ በፍርድ ቤት ወይም በክብር መዝገብ ሹም ዘንድ ይቀመጣል።

፪. ተጋቢዎች ወይም ከተጋቢዎች አንዱ ለማየት በፈለጉ ጊዜ እንዲሁም በፍርድ ቤት ወይም ከተጋቢዎቹ በአንዱ የተፈቀደ ላቸው ሰዎች የውሉን ሰነድ ለማየት ይችላሉ።

## አንቀጽ ፵፮ (፭) ውል ለመዋዋል ስላለው የነፃነት ወሰን

፩. ተጋቢዎች በጋብቻቸው ውል ውስጥ በሌሎች ሦስተኛ ወገኖች ላይ ግዴታን የሚያስከትሉ ስምምነቶችን ማድረግ አይችሉም።

፪. እንዲሁም ተጋቢዎቹ ባሕልን ወይም ሃይማኖትን ወይም የአንድን አገር ሕግ በጥቅሉ በመጥቀስ ብቻ ተስማምተናል በማለት የሚያደርጉት የጋብቻ ውል ውጤት አይኖረውም።

## አንቀጽ ፵፯ (፮) የጋብቻ ውልን ስለማሻሻል

፩. የጋብቻ ውል እንዲሻሻል የቤተሰቡ ጥቅም የሚጠይቅ ሲሆንና ተጋቢዎቹ ሲስማሙ ውሉን በማሻሻል ፍርድ ቤት እንዲያፀድቅ ላቸው መጠየቅ ይችላሉ።

፪. ፍርድ ቤት በተጋቢዎቹ ተሻሽሎ የቀረበው የጋብቻ ውል የቤተሰቡን ጥቅም የማይጎዳ መሆኑን ሲያረጋግጥ የተሻሻለውን ውል ተቀብሎ ያፀድቃል።

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተመለከተው ሁኔታ ፍርድ ቤቱ ውሉን ያፀደቀው እንደሆነ ፣ የተሻሻለው ውል በፍርድ ቤት ወይም በክብር መዝገብ ሹም ዘንድ ይቀመጣል።

## አንቀጽ ፴፰ (፯) የሕግ ተፈፃሚነት

የጋብቻ ውል በሌለ ጊዜ ወይም የጋብቻ ውል ቢኖርም በሕግ ሳይፀና የቀረ እንደሆነ ፣ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ ።

## ክፍል ፪
## ጋብቻ በተጋቢዎች ግላዊ ግንኙነት ላይ ስለሚኖረው ውጤት

## አንቀጽ ፵፱ መከባበር ፣ መተጋገዝና መደጋገፍ

፩· ባልና ሚስት እርስ በርሳቸው መከባበር ፣ መተጋገዝና መደጋገፍ አለባቸው ።

፪· በጋብቻው ውል ውስጥ ይህንን የሚቃረን ስምምነት ማድረግ አይችሉም።

## አንቀጽ ፶ የቤተሰብ የጋራ አመራር (፩) ጠቅላላ

፩· በቤተሰብ አመራር ረገድ ባልና ሚስት እኩል መብት አላቸው።

፪· ባልና ሚስቱ በማናቸውም ረገድ የቤተሰቡን ደህንነትና ጥቅም ለማስጠበቅ ፣ ልጆቻቸው በመልካም ሥነምግባር እንዲታነፁ ፣ ተገቢ ትምህርት እንዲቀስሙና ኃላፊነት የሚሰማቸው ዜጎች ሆነው እንዲያድጉ ለማድረግ መተባበር አለባቸው።

## አንቀጽ ፶፩ (፪) ከተጋቢዎቹ አንዱ ቤተሰቡን ለመምራት ስላለመቻሉ

፩· ከባልና ከሚስት አንደኛው ችሎታ ያጣ ፣ የጠፋ ወይም ቤተሰቡን ጥሎ የሔደ ወይም ከመኖሪያ ሥፍራው በመራቁም ሆነ በማናቸውም ሌላ ምክንያት ፈቃዱን ለመስጠት በማይችልበት ሁኔታ በሚገኝበት ጊዜ ፣ በአንቀጽ ፶ የተመለከተውን የቤተሰብ አመራር አንደኛው ተጋቢ ብቻውን ይፈጽማል።

፪· ባልና ሚስት በጋብቻ ውላቸው ውስጥ ይህንን የሚቃረን ስምምነት ማድረግ አይችሉም።

## አንቀጽ ፶፪ ከጋብቻ በፊት ከሌላ ስለተወለዱ ልጆች

፩· ከባልና ከሚስቱ አንዱ ከጋብቻው በፊት ከሌላ የወለዳቸውን

BACK



ልጆች መልካም አስተዳደግ በሚመለከት በራሱ አሳብና መረነት የፈቀደውን ውሳኔ ለማድረግ ሙሉ መብት ይኖረዋል።

፪· ይህንን የሚቃረን ማናቸውም ስምምነት ውጤት አይኖረውም።

አንቀጽ ፶፫ አብሮ መኖር

፩· ባልና ሚስት አብረው እንዲኖሩ ይገደዳሉ ።

፪· ለጤናቸው አደገኛ ካልሆነ በስተቀር ፣ ባልና ሚስት ከጋብቻ የሚጠበቀውን መደበኛውን የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም አለባቸው።

፫· ይህንን የሚቃረን ማናቸውም ስምምነት ውጤት አይኖረውም።

አንቀጽ ፶፬ የመኖሪያ ሥፍራን ስለመወሰን

ባልና ሚስት የሚኖሩበትን ሥፍራ በጋራ ይወስናሉ።

አንቀጽ ፶፭ በስምምነት ተለያይቶ ስለመኖር

፩· በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፶፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ቢኖርም ፣ ባልና ሚስቱ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ተለያይተው ለመኖር መስማማት ይችላሉ።

፪· ስለዚህ ጉዳይ የተደነገገውን ስምምነት መለወጥ የማይገባ ካልሆነ በስተቀር ፣ ከሁለቱ ተጋቢዎች አንደኛው አስቦ ሊሰርዘው ይችላል።

አንቀጽ ፶፮ የመተማመን ግዴታ

ባል ለሚስቱ ፣ ሚስት ለባልዋ ታማኝ የመሆን ግዴታ አለባቸው ።

ክፍል ፫

ጋብቻ በንብረት በኩል ስለሚኖረው ውጤት

አንቀጽ ፶፯ የባልና ሚስት የግል ሀብት (፩) ያለግብይት የተገኙ ንብረቶች

ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበሯቸው ንብረቶች ወይም ከጋብቻ በኋላ በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው ያገኙዋቸው ንብረቶች የግል ንብረቶቻቸው ሆነው ይቀራሉ ።

BACK



## አንቀጽ ፶፰ (፪) በጋብቻ የተገኙ ንብረቶች

፩· ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ አንዱ የግል ሀብቱ በሆነ ንብረት ለውጥ ያገኘው ወይም በግል ገንዘቡ የገዛቸው ወይም የግል ንብረቱን ሸጦ የሚያገኘው ገንዘብ የግል ሀብቱ ይሆናል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ድንጋጌ ተፈጻሚ የሚሆነው፡ በጋብቻ የተገኘው ንብረት የግል ይባልልኝ ብሎ አንደኛው ወገን ጥያቄ ሲያቀርብ እና ፍርድ ቤት ሲያፀድቀው ብቻ ነው።

## አንቀጽ ፶፱ የግል ሀብትን ስለማስተዳደር (፩) መሠረቱ

፩· እያንዳንዱ ተጋቢ የግል ሀብቱን ራሱ ለማስተዳደርና ገቢውንም ለመቀበል ይችላል።

፪· እያንዳንዱ ተጋቢ የግል ሀብቱን ራሱ ሊያዝበት ነፃነት አለው።

## አንቀጽ ፷ (፪) የግል ሀብት አስተዳደርን በጋብቻ ውል ስለመወሰን

፩· ባልና ሚስት ፡ አንደኛው የሌላውን ተጋቢ የግል ሀብት በሙሉ ወይም በከፊል እንዲያስተዳድርለት እና እንደአስፈላጊነቱ እንዲያዝበት በጋብቻ ውላቸው ሊወስኑ ይችላሉ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው አኳኋን ንብረት የማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው ተጋቢ ፡ በሌላኛው ተጋቢ ሲጠየቅ ስለንብረቱ አስተዳደር ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫ የመስጠት ግዴታ አለበት ።

## አንቀጽ ፷፩ (፫) ስለውክልና ሥልጣን

ከተጋቢዎች አንዱ የግል ሀብቱን በሙሉ ወይም በከፊል እንዲያስተዳድርለት ለሌላኛው ተጋቢ ውክልና መስጠት ይችላል።

BACK



## አንቀጽ ፷፪ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት

፩· ባልና ሚስት ከግል ጥረታቸውና ከግል ወይም ከጋራ ንብረታቸው የሚያገኟቸው ገቢዎች ሁሉ የጋራ ሀብቶቻቸው ይሆናሉ።

፪· በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፶፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የአንደኛው ተጋቢ የግል ሀብት ነው ካልተባለ በስተቀር ፣ ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ በግብይት የሚያገኙት ንብረት ሁሉ የጋራ ሀብታቸው ይሆናል።

፫· በስጦታው ውል ወይም በኑዛዜው ቃል በሌላ አኳኋን ካልተመለከተ በስተቀር ፣ በስጦታ ወይም በኑዛዜ ለተጋቢዎቹ የተሰጧቸው ንብረቶች ሁሉ የጋራ ሀብቶቻቸው ይሆናሉ።

## አንቀጽ ፷፫ የሕግ ግምት

፩· አንደኛው ተጋቢ የግል ሀብቱ መሆኑን ካላስረዳ በስተቀር ማንኛውም ንብረት በአንደኛው ተጋቢ ስም ብቻ የተመዘገበ ቢሆንም እንኳን የጋራ ሀብት እንደሆነ ይቆጠራል።

፪· የግል ንብረት መሆኑን ሦስተኛ ወገኖች የሚያውቁት ወይም ሊያውቁት የሚገባ ካልሆነ በስተቀር ፣ ባልና ሚስቱ ወይም ከሁለቱ አንዱ ይዞው ንብረት የግል ነው በማለት በሦስተኛ ወገን ላይ መቃወሚያ አድርገው ሊያቀርቡት አይችሉም።

## አንቀጽ ፷፬ ስለባልና ሚስት ገቢ (፩) መደበኛ የገቢ አስተዳደር

፩· ባልና ሚስት እያንዳንዳቸው ገቢያቸውን በየራሳቸው ይቀበላሉ።

፪· ባልና ሚስት በየግላቸው የሚያገኙትን ገቢ ፣ የግል ወይም የጋራ የባንክ ሂሳብ በመክፈት ማስቀመጥ ይችላሉ።

፫· ከባልና ከሚስት አንደኛው ሲጠይቅ ፣ ሌላኛው ተጋቢ ያገኘውን የገቢ መጠን የማስታወቅ ግዴታ አለበት ።

BACK



## አንቀጽ ፷፭ (፪) ልዩ ሁኔታ

፩· ከባልና ከሚስት አንዱ ፡ ገቢውን ሌላኛው ተጋቢ እንዲቀበለለት ሥልጣን ለመስጠት ሙሉ ነፃነት አለው።

፪· ከባልና ከሚስት በአንደኛው ጠያቂነት የአንደኛውን ገቢ ሌላኛው ተጋቢ እንዲቀበልና ለመቀበሉም ደረሰኝ እንዲሰጥ ፍርድ ቤት ሊወስን ይችላል።

፫· በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ፡ ከባልና ከሚስት የአንደኛው ገቢ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲከበር በፍርድ ቤት ሊታዘዝ ይችላል።

## አንቀጽ ፷፮ የጋራ ሀብትን ስለማስተዳደር

፩· ከባልና ከሚስት አንዱ ፡ የጋራ ሀብታቸውን በሙሉ ወይም በከፊል እንዲያስተዳድር ግልጽ ስምምነት ከሌለ በስተቀር፣ ባልና ሚስቱ የጋራ ሀብታቸውን በጋራ ያስተዳድራሉ።

፪· ከባልና ከሚስት አንዱ ፡ ችሎታ የለውም ተብሎ ሲወሰን ወይም ንብረት የማስተዳደር መብቱን ሲገፈፍ ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት የጋራ ሀብታቸውን ለማስተዳደር የማይችል ሆኖ ሲገኝ ሌላኛው ተጋቢ የጋራ ሀብቱን የማስተዳደሩን ተግባር ያከናውናል።

## አንቀጽ ፷፯ የማስታወቅ ግዴታ

ከተጋቢዎች አንዱ ብቻ የጋራ ሀብታቸውን በሚያስተዳድርበት ጊዜ የሀብቱን አስተዳደር በተመለከተ፣ ለሌላኛው ተጋቢ መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት ።

BACK



## አንቀጽ ፷፰ (፩) የተጋቢዎች ስምምነት አስፈላጊ ስለመሆኑ

በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ፣ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የተጋቢዎቹ ስምምነት አስፈላጊ ነው፤

ሀ) የጋራ የሆነውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥ ፣ ለመለወጥ ፣ ለማከራየት ፣ በመያዣ ወይም በዋስትና ለመስጠት ወይም በሌላ በማናቸውም ሁኔታ በዚሁ ንብረት ላይ ሌሎች ሰዎች መብት እንዲያገኙ ለማድረግ ፣

ለ) ዋጋቸው ከብር ፭፻ (አምስት መቶ) በላይ የሆኑ የሚንቀሳቀሱ የጋራ ንብረቶችን ወይም የገንዘብ ሰነዶችን ፣ ለመሸጥ ፣ ለመለወጥ በመያዣ ወይም በዋስትና ለመስጠት ወይም በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ለማስተላለፍ፤

ሐ) ከብር ፩፻ (አንድ መቶ) በላይ ዋጋ ያለውን የጋራ ንብረት ወይም ገንዘብ ለሌላ ሰው በስጦታ ለማስተላለፍ ፤

መ) ከብር ፭፻ (አምስት መቶ) በላይ ለመበደር ወይም ለማበደር ወይም ለሌላ ሰው ዋስ ለመሆን።

## አንቀጽ ፷፱ (፪) የስምምነት አለመኖር ስለሚያስከትለው ውጤት

፩· አንደኛው ተጋቢ ከዚህ በላይ የተመለከተውን ድንጋጌ ባለማክበር የውል ግዴታ ገብቶ የተገኘ እንደሆነ ፣ ሌላኛው ተጋቢ ለፍርድ ቤት በሚያቀርበው ጥያቄ ግዴታው ሊፈርስ ይችላል።

፪· ግዴታው እንዲፈርስ የሚቀርበው ጥያቄ ጠያቂው ወገን ግዴታው መገባቱን ከአወቀበት ቀን ጀምሮ ከስድስት ወር በኋላ ወይም በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ግዴታው ከተገባ ከሁለት ዓመት በኋላ ሊቀርብ አይችልም።

## አንቀጽ ፸ የባልና ሚስት ዕዳ

፩· ከባል ወይም ከሚስት በግል የሚጠየቅ ዕዳ ፣ ከባለዕዳው ተጋቢ የግል ሀብት ፣ የግል ሀብቱ ዕዳውን ለመሸፈን በቂ በማይሆንበት ጊዜ ከጋራ ሀብታቸው ይከፈላል።

BACK



፪· ዕዳው የመጣው ለትዳራቸው ጥቅም ከሆነ ከጋራ ሀብታቸው ፣ የጋራ ሀብታቸው ዕዳውን ለመሸፈን በቂ በማይሆንበት ጊዜ ከባል ወይም ከሚስት የግል ሀብት ይከፈላል።

## አንቀጽ ፸፩ ለትዳር ጥቅም እንደተደረገ የሚቆጠር ዕዳ

የሚከተሉት ዕዳዎች ለትዳር ጥቅም እንደተደረጉ የሚቆጠሩ ናቸው፤

ሀ) ለባልና ለሚስት እንዲሁም ለልጆቻቸው የዕለት ኑሮ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ለማሟላት የተገቡ ዕዳዎች፤

ለ) ባል ወይም ሚስት ቀለብ ለመስጠት ያለባቸውን ግዴታ ለመወጣት የተደረጉ ወጪዎች፣

ሐ) ከባልና ከሚስት በአንደኛው ወይም በዕዳ ጠያቂው አመልካችነት ለትዳር ጥቅም ስለመሆኑ ፍርድ ቤት የተቀበለው ሌላ ዕዳ።

## አንቀጽ ፸፪ የትዳር ወጪዎችን ስለመሸፈን

ተጋቢዎች የትዳራቸውን ወጪ ለመሸፈን እያንዳንዳቸው እንደየአቅማቸውና ችሎታቸው አስተዋጽኦ ማድረግ አለባቸው ።

## አንቀጽ ፸፫ በተጋቢዎች መካከል ስለሚደረጉ ውሎች

ባልና ሚስቱ ተጋብተው በሚኖሩበት ጊዜ በመካከላቸው የሚያደርጓቸው ውሎች፣ ፍርድ ቤት ካላፀደቃቸው በስተቀር ውጤት አይኖራቸውም።

## ምዕራፍ አራት
## ስለጋብቻ መፍረስ

### አንቀጽ ፸፬ በማናቸውም ዓይነት የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት የተቋቋሙ ጋብቻዎች እኩል ስለመሆናቸው

፩· ጋብቻው የተፈጸመበት ሥርዓት ማናቸውም ዓይነት ቢሆን ፣ የጋብቻው መፍረስና የሚያስከትለው ውጤት አንድ ዓይነት ነው።

፪· ጋብቻው የተፈፀመው በማናቸውም የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት ቢሆንም ፣ የጋብቻውን መፍረስ በተመለከተ ማናቸውም ልዩነት አይደረግም።

### አንቀጽ ፸፭ ጋብቻ ስለሚፈርስባቸው ምክንያቶች

ጋብቻ የሚፈርሰው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፤

ሀ) ከተጋቢዎቹ አንዱ ሲሞት ወይም በፍርድ ቤት የመጥፋት ውሳኔ ሲሰጥ ፣ ወይም

ለ) ጋብቻ ለመፈፀም መሟላት ካለባቸው ሁኔታዎች አንዱ በመጣሱ ምክንያት በሕግ መሠረት ጋብቻው እንዲፈርስ ሲወሰን፣ ወይም

ሐ) የፍቺ ውሳኔ ሲሰጥ።

### አንቀጽ ፸፮ ፍቺ ስለሚወሰንበት ሁኔታ

ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ ሊወሰን የሚችለው ፣

ሀ) ባልና ሚስት በስምምነት ለመፋታት ሲወስኑና ይህንኑ ለፍርድ ቤት አቅርበው ውሳኔያቸው ተቀባይነት ሲያገኝ ፣ ወይም

ለ) ከተጋቢዎቹ አንዱ ወይም ሁለቱ ተጋቢዎች በአንድነት ጋብቻቸው በፍቺ እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ሲያቀርቡ ነው።

## ክፍል ፩
## በስምምነት ስለመፋታት

### አንቀጽ ፸፯ በስምምነት ለመፋታት ስለሚቀርብ ጥያቄ

፩· ባልና ሚስት በስምምነት ለመፋታት የወሰኑ እንደሆነ ፡ የፍቺ ስምምነታቸውንና ፍቺው የሚያስከትለውን ውጤት በጽሑፍ ለፍርድ ቤት በማቅረብ ፍቺው እንዲፀድቅላቸው መጠየቅ ይችላሉ ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)/ የተመለከተው ቢኖርም፣ ተጋብተው ስድስት ወር ያልሞላቸው ባልና ሚስት በስም ምነት ለመፋታት አይፈቀድላቸውም።

፫· ባልና ሚስት ለፍርድ ቤት በሚያቀርቡት የፍቺ ስምምነት ላይ ለመፋታት የወሰኑበትን ምክንያት እንዲገልጹ አይገደዱም።

### አንቀጽ ፸፰ የፍርድ ቤት ሥልጣን

፩· በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፸፯ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው ድንጋጌ መሠረት የመፋታት ጥያቄ ሲቀርብለት ፍርድ ቤቱ ባልና ሚስቱን በተናጠል ወይም በአንድ ላይ በማስቀረብ ስለጥያቄያቸው ያነጋግራቸዋል ፡ እንዲሁም የመፋታት ሀሳባ ቸውን እንዲለውጡ ይጠይቃቸዋል ።

፪· ባልና ሚስት የመፋታት ሀሳባቸውን የማይለውጡ መሆኑን የገለጹ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ ከሶስት ወር የማይበልጥ የማሰላሰያ ጊዜ በመወሰን ሊያሰናብታቸው ይችላል።

### አንቀጽ ፸፱ ጉዳዩን እንደገና ስለማንቀሳቀስ

፩· ባልና ሚስቱ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፸፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው የማሰላሰያ ጊዜ ቢሰጣቸውም እንኳን በመፋ ታት ሃሳባቸው የፀኑ እንደሆነ ፡ የተሰጣቸው የማሰላሰያ ጊዜ

BACK



ከአቤቱታቡ ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ጉዳያቸውን እንደገና በማንቀሳቀስ የፍቺ ስምምነታቸውን እንዲያፀድቅ ላቸው ፍርድ ቤቱን መጠየቅ ይችላሉ ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው የስድስት ወር የጊዜ ገደብ ቢኖርም ፡ ባልና ሚስቱ አዲስ የፍቺ ስምምነት ከማቅረብ የሚያግዳቸው አይሆንም።

## አንቀጽ ፹ የፍቺ ስምምነቱን ስለማጽደቅ

፩· ፍርድ ቤቱ የፍቺ ስምምነቱን የሚያፀድቀው የባልና ሚስቱ ትክክለኛ ፍላጐት መሆኑን እና ባልና ሚስቱ ፈቃዳቸውን በነፃ የሰጡ መሆኑን ፡ እንዲሁም ስምምነቱ ከሕግና ሞራል ጋር የማይቃረን መሆኑን ሲያምን ብቻ ነው ።

፪· ፍርድ ቤቱ የፍቺውን ስምምነት ያፀደቀው እንደሆነ ስለፍቺው ውጤት ያደረጉትንም ስምምነት አብሮ ያፀድቃል።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው ቢኖርም ፡ ባልና ሚስቱ ስለፍቺው ውጤት ያደረጉት ስምምነት የልጆቻቸውን ደህንነትና ጥቅም በበቂ ሁኔታ የማያስጠብቅ ወይም የአንደኛውን ተጋቢ ጥቅም የሚጐዳ ሆኖ ካገኘው ፡ ፍርድ ቤቱ የፍቺውን ስምምነት ብቻ በማጽደቅ የፍቺውን ውጤት በተመለከተ ጉድለቶቹ እንዲስተካከሉ ተገቢ መስሎ የታየውን ውሳኔ ይሰጣል ።

## ክፍል ፪
## ጥያቄ በመቅረቡ ምክንያት ስለሚወሰን ፍቺ

## አንቀጽ ፹፩ (፩) የፍቺ ጥያቄ ስለማቅረብ

፩· ከባልና ሚስት አንደኛው ወይም ሁለቱም ተጋቢዎች በአንድነት በመሆን፡ ጋብቻቸው በፍቺ እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ ።

፪· ከባልና ሚስት አንደኛው ወይም ሁለቱም ተጋቢዎች በአንድነት በመሆን የፍቺ ጥያቄ ሲያቀርቡ ፍቺ ለመጠየቅ

ምክንያት የሆናቸውን ጉዳይ መግለጽ ይችላል ።

## አንቀጽ ፹፪ (፪) የፍርድ ቤት ሥልጣን

፩· በዚህ ሕግ አንቀጽ ፹፩ መሠረት ጋብቻው በፍቺ እንዲፈርስ ጥያቄ ሲቀርብለት፣ ፍርድ ቤቱ ባልና ሚስቱን በተናጠልም ሆነ በአንድነት በማነጋገር የፍቺው ጥያቄ የሚቀርበትንና አለመግባባቱን በስምምነት ለመፍታት የሚችሉበትን ሁኔታ ለመፍጠር እንዲችሉ ያግባባቸዋል ።

፪· ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው መሠረት ምክር ውጤት ያላገኘ እንደሆነ ወይም እንደነገሩ ሁኔታ ውጤት የማያገኝ መስሎ የታየው እንደሆነ ፡ ባልና ሚስቱ ከፍርድ ቤት ውጭ ራሳቸው በሚመርጧቸው ሽማግሌዎች አማካይነት ጉዳያቸውን በዕርቅ እንዲጨርሱ ሊጠይቃቸው ይችላል ።

፫· ባልና ሚስቱ ጉዳያቸውን በሽማግሌ አማካይነት በዕርቅ ለመጨረስ ያልተስማሙ እንደሆነ፣ ፍርድ ቤቱ ከሦስት ወር ያልበለጠ የማሰላሰያ ጊዜ በመወሰን ሊያሰናብታቸው ይችላል።

፬· ከዚህ በላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ተገቢውን ሁሉ አድርጎ ጥረቱ ውጤት ያላስገኘ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የአስታራቂ ሽማግሌዎች ሪፖርት ከደረሰው ወይም እንደሁኔታው ለተጋቢዎቹ የተወሰነው የማሰላሰያ ጊዜ ከአበቃበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የፍቺ ውሳኔ ይሰጣል ።

፭· የፍቺ አቤቱታው እንደቀረበ ፍርድ ቤቱ ወዲያውኑ ባልና ሚስቱ ስለሚተዳደሩበትና ስለሚኖሩበት ሁኔታ ፡ ስለልጆቻቸው አጠባበቅ ፡ ስለሚኖሩበት ስፍራና ስለአኗኗራቸው እንዲሁም ስለንብረታቸው አስተዳደር ተገቢ መስሎ የታየውን ትዕዛዝ ይሰጣል ።

፯· ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) በተመለከተው መሠረት ትዕዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ ከሁለቱ ተጋቢዎች የአንዳቸው ከጋራ መኖሪያቸው መውጣት የግድ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የጋራ መኖሪያቸውን ለቆ ቢወጣ የባሰ ጉዳት የማይደርስበት ወገን የትኛው መሆኑን እንዲሁም የልጆቻቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ አመቺ የሚሆነውን ሁኔታ ሁሉ ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል ።

## አንቀጽ ፹፫ የፍቺ ውጤቶችን ስለመወሰን

፩· በዚህ ክፍል መሠረት ጋብቻው በፍቺ የፈረሰ እንደሆነ ፣ ፍርድ ቤቱ ፍቺው ስለሚያስከትለው ውጤት እንዲስማሙ ባልና ሚስቱን ይጠይቃቸዋል ።

፪· ባልና ሚስቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለመስማማት ያልፈለጉ ወይም ለመስማማት ሞክረው ስምምነት ላይ ለመድረስ ያልቻሉ እንደሆነ ፣ ፍርድ ቤቱ በራሱ ወይም በሽማግሌዎች ወይም ፍርድ ቤቱ በሚሾማቸው ባለሞያዎች አማካይነት ወይም አመቺ መስሎ በሚታየው በማናቸውም ዘዴ የፍቺውን ውጤት ይወስናል ።

፫· የፍቺው ውጤት በስምምነት በሚያልቅበት ወይም በሽማግሌዎች ወይም በባለሞያዎች በሚወሰንበት ጊዜ ውሳኔው ተፈፃሚነት የሚኖረው ለፍርድ ቤቱ ቀርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ ነው።

፬· ፍርድ ቤቱ ፍቺውን አስቀድሞ በመወሰን የፍቺውን ውጤት በተመለከተ የሚሰጠውን ውሳኔ እንደሁኔታው ከፍቺ በኋላ ከ፮ ወር ላልበለጠ ጊዜ ሊያዘገየው ይችላል ።

## አንቀጽ ፹፬ ስለ ካሳ

ከባልና ከሚስት አንዱ ለፍቺው ምክንያት የሆነውን በደል ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነና ፍርድ ቤቱ ለፍትህ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው

BACK



በሌላው ተጋቢ ላይ ለደረሰው ጉዳት በዳዩ ተመጣጣኝ የሆነ ካሣ እንዲከፍል ሊወስን ይችላል።

## ምዕራፍ አምስት

## የባልና ሚስትን ሀብት ስለማጣራት

### አንቀጽ ፹፫ የባልና ሚስትን ሀብት በስምምነት ስለማጣራት

፩· በዚህ ሕግ ስለካሣ ክፍያ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ፡ ጋብቻው በዚህ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የፈረሰ እንደሆነ ፡ ባልና ሚስቱ የጋብቻቸው መፍረስ በንብረት በኩል የሚያስከት ለውን ውጤት አስመልክተው በሚያደርጉት ስምምነት ወይም በጋብቻ ውላቸው መሠረት ይጣራል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው የጋብቻ ውል ወይም ስምምነት የሌለ ወይም በሕግ ፊት የማይፀና ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ፡ የባልና ሚስት ሀብት በሚከተሉት ድንጋጌዎች መሠረት ይጣራል።

### አንቀጽ ፹፬ የግል ሀብትን መልሶ ስለመውሰድ

፩· ባል ወይም ሚስት የግሉ መሆኑን በማስረዳት የግል ሀብቱ የሆነውን ንብረቱን መልሶ የመውሰድ መብት ይኖረዋል ።

፪· ከባልና ሚስቱ አንደኛው የግል ሀብቱ የሆነ ማናቸውም ንብረት ለሌላ ሰው የተላለፈ መሆኑንና ከዚሁ ግብይት የተገኘውም ገንዘብ ከጋራ ሀብታቸው ጋር የተቀላቀለ መሆኑን ያስረዳ እንደሆነ፡ ከዚህ ንብረት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ገንዘብ ወይም ንብረት ከጋራ ሀብታቸው በቅድሚያ የማንሳት መብት ይኖረዋል።

፫· ባልና ሚስት የየግል ሀብታቸውን የሚያነሱበት ሁኔታ ሲኖር ሁለቱም በመጨረሻ ከተገኘው የንብረት መጠን እንደየአስተ ዋጽኦዋቸው ሊደርሳቸው የሚችለውን ያህል የማንሳት መብት ይኖራቸዋል።

## አንቀጽ ፹፯ ስለካሳ

፩· በዚህ ሕግ መሠረት የጋራ ንብረቱን ወይም የሌላኛውን ተጋቢ ንብረት በብቸኝነት እንዲያስተዳድር ሥልጣን የተሰጠው ተጋቢ ፡ ከተሰጠው ሥልጣን ውጪ በፈፀማቸው ድርጊቶች ምክንያት ወይም ከብልሹ አስተዳደር የተነሳ ወይም የካሳ ጠያቂውን መብት በማታለል ድርጊቱ የጎዳ እንደሆን ፡ ፍርድ ቤቱ በተበዳዩ ጥያቄ ሲቀርብለት ተገቢ የጉዳት ካሳ እንዲከፈለው ሊያዝ ይችላል ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቀርብ የካሳ ጥያቄ ፡ ተፈፀመ የተባለው ድርጊት ጋብቻው ከመፍረሱ ከአምስት ዓመት በፊት የሆነ እንደሆን ፡ ተቀባይነት አይኖረውም ።

## አንቀጽ ፹፰ ያለአግባብ ስለመበልጸግ

ባልና ሚስት ተቃራኒ ስምምነት ካላደረጉ በስተቀር፡ ከባልና ሚስት የአንደኛው የግል ሀብት ከሆነ ንብረት የሌላኛው የግል ሀብት ወይም የጋራ ሀብታቸው ያለአግባብ መበልጸጉን ያስረዳ እንደሆን፡ ፍርድ ቤቱ ተገቢ ካሳ እንዲከፈለው ሊያዝ ይችላል።

## አንቀጽ ፹፱ የዕዳ ጠያቂዎችን መብት ስለማክበር

ከባልና ሚስት አንደኛው ወይም ሁለቱም በጋራ በፍርድ የተረጋገጠ ባቸው ወይም ሁለቱም ያመኑት ዕዳ መኖሩ የታወቀ እንደሆን ፡ ይኸው ዕዳ የባልና ሚስት ሀብት ከመከፋፈሉ በፊት ተቀንሶ የሚከፈል ይሆናል።

BACK



## አንቀጽ ፺ (፩) የጋራ ሀብትን ስለማከፋፈል

ከዚህ በላይ የተመለከቱትና የባልና ሚስት ሀብትን በስምምነት ስለማከፋፈል የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ፡ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ለሁለቱም እኩል የሚከፋፈል ይሆናል ።

## አንቀጽ ፺፩ (፪) የባልና ሚስት ሀብት በዓይነት የሚከፋፈል ስለመሆኑ

፩· በመሠረቱ ፡ እያንዳንዱ ተጋቢ ከጋራ ሀብቱ የተወሰነ ንብረት እንዲደርሰው በማድረግ የጋራ ሀብቱ በዓይነት እንዲከፋፈል ይደረጋል ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው አኳኋን እኩል ለማከፋፈል የማይቻል ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ፡ ልዩነቱ በገንዘብ እንዲካካስ ይደረጋል ።

፫· የሀብት ክፍፍሉ በሚደረግበት ጊዜ እያንዳንዱ ተጋቢ ይበልጥ ጠቃሚነት ያላቸውን ንብረቶች እንዲያገኝ ለማድረግ ጥረት መደረግ ይኖርበታል።

## አንቀጽ ፺፪ ለማከፋፈል አዳጋች ስለሆኑ ንብረቶች

፩· ንብረቱ ለክፍፍል የማያመች ወይም ለማከፋፈል የማይቻል ሆኖ የተገኘ እንደሆነና ባልና ሚስቱን ንብረቱ ከሁለቱ ለአንዳቸው እንዲሰጥ ለማስማማት ሳይቻል የቀረ እንደሆነ ንብረቱ ተሸጦ የተገኘውን ገንዘብ እንዲከፋፈሉ ይደረጋል።

፪· ስለአሻሻጡ ሁኔታ ባልና ሚስቱ ሳይስማሙ ቀርተው አንደኛው ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ ሽያጩ የሚደረገው በሐራጅ ይሆናል ።

BACK



## አንቀጽ ፶፫ ጋብቻው ከፈረሰ በኋላ ከባልና ሚስት ስለሚጠየቅ ዕዳ

፩· ጋብቻው ከፈረሰና የባልና ሚስት ሀብት ከተከፋፈለ በኋላ የሚጠየቅ ዕዳ በጋራ መከፈል የነበረበት በሆነ ጊዜ ፤ ስለዕዳው አከፋፈል ሁለቱም በየድርሻቸው መጠን ተጠያቂ ይሆናሉ ።

፪· ዕዳው የሚመለከተው አንደኛውን ተጋቢ በሆነ ጊዜ ፤ የዕዳው ክፍያ ሊጠየቅ የሚችለው ባለዕዳ ከሆነው ተጋቢ ብቻ ይሆናል።

## ምዕራፍ ስድስት
## ጋብቻ ለመፈፀሙ ስለሚቀርብ ማስረጃ

## አንቀጽ ፺፬ የጋብቻ ምስክር ወረቀት

ጋብቻ መፈፀሙን ለማስረዳት የሚቻለው ጋብቻው በተፈፀመበት ዕለት ወይም ከዚያ በኋላ በሕጉ መሠረት ተዘጋጅቶ የተሰጠውን የጋብቻ የምስክር ወረቀት በማቅረብ ነው ።

## አንቀጽ ፺፭ የጋብቻ ምስክር ወረቀት በሌለ ጊዜ ስለሚቀርብ ማስረጃ

የጋብቻ ምዝገባ ሳይደረግ የቀረ ወይም መዝገቡ በመጥፋቱ ምክንያት ጋብቻ መፈፀሙን በጋብቻ ምስክር ወረቀት ለማስረዳት ያልተቻለ እንደሆነ ፡ ጋብቻ ለመፈፀሙ የትዳር ሁኔታ መኖሩን በማረጋገጥ ማስረዳት ይቻላል ።

## አንቀጽ ፺፮ የትዳር ሁኔታ መኖር (፩) ትርጓሜ

አንድ ወንድና አንዲት ሴት የትዳር ሁኔታ አላቸው የሚባሉት ፡ ራሳቸውን እንደባልና ሚስት የሚቆጥሩና የሚኖሩ ከመሆናቸውም በላይ ቤተዘመዶቻቸውና ማኅበረሰቡ እንደባልና ሚስት የሚቀበሏቸው ሆነው ሲገኙ ነው።

BACK



## አንቀጽ ፺፺ (፪) ጋብቻ ለመፈፀሙ የትዳር ሁኔታ መኖርን ስለማስረዳት

፩· ከዚህ በላይ በተመለከተው አንቀጽ መሠረት አንድ ሰው በራሱና ከእርሱ ጋር ጋብቻ አለኝ ከሚለው ወገን ጋር የትዳር ሁኔታ መኖሩን ለማስረዳት የቻለ እንደሆነ ፤ ፍርድ ቤቱ ጋብቻ ተፈጽሟል ሲል የሕግ ግምት ይወስዳል ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን ግምት፣ ጋብቻው አለመፈፀሙን ማናቸውንም ዓይነት አስተማማኝ ማስረጃ በማቅረብ ለማፍረስ ይቻላል ።

## ምዕራፍ ሰባት

## ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ ስለመኖር

## አንቀጽ ፺፰ (፩) ትርጓሜ

ጋብቻ ሳይፈፅሙ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ማለት አንድ ወንድና አንዲት ሴት በሕግ በሚፀና አኳኋን ጋብቻ ሳይፈጽሙ በትዳር መልክ የኖሩ ሲሆን ነው ።

## አንቀጽ ፺፱ (፪) ማብራሪያ

፩· ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው ኖሩ ለማለት ወንድየውና ሴትየዋ የሚያሳዩት ሁኔታ በሕግ እንደተጋቡ ሰዎች ዓይነት መሆኑ አስፈላጊና በቂ ነው ።

፪· ለሶስተኛ ወገኖች እንደተጋቡ ሆነው መቅረብ አስፈላጊ አይደለም ።

፫· አንድ ወንድና አንዲት ሴት በታወቀና በተደጋገመ ሁኔታ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት መፈፀማቸው ብቻ፣ በሁለቱ መካከል ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት ግንኙነት አላቸው ለማለት በቂ ምክንያት አይደለም ።

BACK



## አንቀጽ ፩፻ የጋብቻ ዝምድና የማያስከትል ስለመሆኑ

፩· ጋብቻ ሳይፈፅሙ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር፣ በወንድ የውና በሴቲቱ የሥጋ ዘመዶች መካከል እንዲሁም በሴትየዋና በወንድየው የሥጋ ዘመዶች መካከል እንዳችም የጋብቻ ዝምድና አያስከትልም ።

፪· ሆኖም የጋብቻ ዝምድና ባለ ጊዜ፣ ጋብቻን የሚከለክሉ ድንጋጌዎች፣ ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ባለ ጊዜም ተፈፃሚ ይሆናሉ ።

## አንቀጽ ፩፻፩ የጋራ ኑሮ ወጪዎችን ስለመሸፈን

ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ሰዎች የጋራ ኑሮአቸውን ወጪ ለመሸፈን እያንዳንዳቸው እንደየአቅማቸውና ችሎታቸው አስተዋጽኦ ማድረግ አለባቸው።

## አንቀጽ ፩፻፪ ስለ ጋራ ሀብት

፩· የንብረት አስተዳደራቸውን አስመልክቶ የሚያደርጉት ውል እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ሰዎች ከሶስት ዓመት ላላነሰ ጊዜ አብረው ከኖሩ፣ በግንኙነቱ ውስጥ እያሉ ያፈሩዋቸው ንብረቶች የጋራ ሀብታቸው ይሆናል ።

፪· ተቃራኒ ማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ አብረው በመኖር ላይ እያሉ የሚኖሯቸው ንብረቶች በግንኙነቱ ውስጥ የተፈሩ ሀብቶች ተደርገው ይቆጠራሉ ።

፫· ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ወንድና ሴት የሚገቧቸው ዕዳዎች አብረው በሚኖሩበት ጊዜ ለጋራ ኑሮአቸው ወይም ከግንኙነቱ የተወለዱ ልጆችን መሠረታዊ ፍላጎቶች ለማሟላት ሲባል የተገቡ ዕዳዎች ሲሆኑ፣ ለዕዳዎቹ አከፋፈል ሁለቱም በአንድነትና በነጠላ

ኃላፊዎች ይሆናሉ ።

**አንቀጽ ፩፻፫ የጋራ ንብረት ስለሚያስከትለው ውጤት**

በዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው መሠረት የጋራ ሀብት በሚፈጠርበት ጊዜ ስለንብረቱ አስተዳደር፣ የሶስተኛ ወገን ዕዳ አከፋፈልና ንብረት ማጣራት ሂደት በዚህ ሕግ በጋብቻ ስለሚፈጠር የጋራ ንብረትና የማጣራት ሂደት የተነገሩት ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል ። (አንቀጽ ፹፮–፺፫)

**አንቀጽ ፩፻፬ የልጆች መወለድ**

ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብረው ከሚኖሩ ወንድና ሴት የተወለዱት ልጆች ተወላጅነታቸው የሚረጋገጠው በዚህ ሕግ ስለ መወለድ በተባለው ምዕራፍ ውስጥ በተደነገገው መሠረት ይሆናል።

**አንቀጽ ፩፻፭ የግንኙነት መቋረጥ**

፩· ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ወንድና ሴት በማንኛውም ጊዜ ግንኙነታቸው እንዲቋረጥ ማድረግ ይችላሉ ።

፪· በዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፪ ስለጋራ ሀብት የተነገረው እንደተጠበቀ ሆኖ ፡ ግንኙነቱ እንዲቋረጥ ያደረገው ወገን ጥፋት ካልፈጸመ በስተቀር ካሳ እንዲከፍል አይገደድም።

**አንቀጽ ፩፻፮ የግንኙነቱ ማስረጃ**

፩· ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖርን ፤ የግንኙነቱ ሁኔታ መኖሩን በማረጋገጥ ማስረዳት ይቻላል ።

፪· አንድ ወንድና አንዲት ሴት ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው ይኖራሉ የሚባለው ምንም እንኳን በሕግ የተጋቡ ባይሆኑም የተጋቡ ሰዎችን ሁኔታ ሲያሳዩና ቤተዘመዶቻቸውና ማኅበረሰቡ እንደተጋቡ ሰዎች የሚኖሩ ናቸው ብለው ሲገምቷቸው ነው።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው ሁኔታ መኖሩን

BACK



አንደኛው ወገን ለማስረዳት የቻለ እንደሆነ ፤ ፍርድ ቤቱ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ናቸው ሲል የሕግ ግምት ይወስዳል ።

፬· ከዚህ በላይ የተመለከተውን የሕግ ግምት ማናቸውንም ዓይነት አስተማማኝ ማስረጃ በማቅረብ ግንኙነት ያለመኖሩን በማስረዳት ማፍረስ ይቻላል ።

አንቀጽ ፩፻፯ ጋብቻ ሳይፈጸም የሚደረጉ ሌሎች ግንኙነቶች

፩· ከጋብቻ ሥርዓት ወይም ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ ከመኖር ውጪ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል የሚደረጉ ሌሎች ግንኙነቶች በሕግ ፊት ምንም ውጤት አይኖራቸውም ።

፪· በዚህ ሕግ ስለ ጉዲፈቻ ልጅ ወይም ልጅነትን ስለመቀበል የተወሰኑት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፤ ከእንደዚህ ያለ ግንኙነት የተወለዱ ልጆች ከእናታቸው በስተቀር ከሌላ ሰው ጋር ማናቸውም ዓይነት ህጋዊ ግንኙነት አይኖራቸውም።

ምዕራፍ ስምንት

በጋብቻ እና ጋብቻ ሳይፈፀም እንደ ባልና ሚስት አብሮ በመኖር

የሚነሱ ክርክሮችን ስለመወሰን

ክፍል ፩

ጠቅላላ

አንቀጽ ፩፻፰ ተፈጻሚነት ስለሚኖረው ሕግ

በዚህ ሕግ የተመለከቱት የሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ፤ በዚህ ሕግ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ለሚነሱ ክርክሮች የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል ።

## አንቀጽ ፩፻፱ የባልና ሚስትን ሃብት ስለማጣራት የተደነገጉት ተፈጻሚ ስለመሆናቸው

፩· ጋብቻው የፈረሰው በፍቺ ባይሆንም፣ የባልና ሚስትን ሀብት ስለማጣራት ከዚህ በላይ በምዕራፍ ፫ የተደነገጉት እንደየአግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ ።

፪· በተለይም ጋብቻው የፈረሰው በሞት በሆነ ጊዜ፣ በሕይወት ባለው ተጋቢ እና በሟች ወራሾች መካከል የንብረት ክፍፍልን በተመለከተ ክርክር የተነሳ እንደሆነ፣ የባልና ሚስትን ሀብት ስለማጣራት በዚህ ሕግ በምዕራፍ ፫ የተደነገጉት እንደየአግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ ።

## አንቀጽ ፩፻፲ የባልና ሚስት ክርክር ስለሚታይበት ሁኔታ

ፍርድ ቤት የባልና ሚስትን ክርክር በሚያይበት ጊዜ እንደነገሩ ሁኔታ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው፣ ባልና ሚስቱን በአንድነት ወይም በተናጠል ሲያነጋግር፣ ወይም ጉዳዩን ሲመረምርና ምስክር ሲሰማ በዝግ ያስችላል።

## አንቀጽ ፩፻፲፩ ስለ ውሳኔ አሰጣጥ

ፍርድ ቤቱ አስፈላጊና ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ፍቺ በሚወስንበት ጊዜ የተጋቢዎችን ወይም የቤተዘመዶቻቸውን መልካም ስም ለመጠበቅ ዝርዝር ጉዳዮችን ከመተቸት በመቆጠብ ፍቺውን ለመወሰን የሚያስችሉ ምክንያቶች መኖራቸውን ብቻ በውሳኔው ላይ ሊያሰፍር ይችላል ።

## አንቀጽ ፩፻፲፪ ስለ ይግባኝ

ፍርድ ቤቱ ፍቺ መወሰኑን ብቻ መሠረት በማድረግ ይግባኝ መጠየቅ አይቻልም ።

## አንቀጽ ፩፻፲፫ የልጆችን አጠባበቅና አያያዝ በሚመለከት ፍርድ ቤቱ ስለሚሰጠው ውሳኔ

፩· ፍርድ ቤቱ ጋብቻው እንዲፈርስ ሲወስን ልጆች ከማን ጋር ሊኖሩ እንደሚገባ ፣ ስለትምህርታቸው እና ስለጤናቸው

አጠባበቅ ፣ ስለቀለባቸውና ባጠቃላይም ስለአኗኗራቸው እንዲሁም ወላጆችና ልጆቻቸው ለመጠያየቅ ስላላቸው መብት መወሰን አለበት ፡፡

፪· ፍርድ ቤቱ ከዚህ በላይ በተመለከተው ሁኔታ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ፣ የወላጆችን የገቢ ፣ የዕድሜ፣ የጤና እና የአኗኗር ሁኔታ እንዲሁም የልጆቹን ዕድሜ ፣ ጥቅማቸውና ፍላጐታቸው የሚጠበቅበትን ሁኔታ ማገናዘብ ይኖርበታል ፡፡

፫· ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ መሠረት ስለልጆች አያያዝና አጠባበቅ የሚሰጠው ውሳኔ የሁኔታዎች መለወጥን ምክንያት በማድረግ በሚቀርብ ጥያቄ ሊሻሻል ወይም ሊለወጥ ይችላል፡፡

አንቀጽ ፩፻፲፬ ጋብቻ ሳይፈፀም እንደ ባልና ሚስት አብሮ ስለመኖር

በዚህ ክፍል የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደየአግባብነታቸው ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብረው በሚኖሩ ሰዎችም ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ ፡፡

## ክፍል ፪
## ስለ ፍርድ ቤት ሥልጣን

አንቀጽ ፩፻፲፭ የሚጸና ጋብቻ ስለመኖሩ

ጋብቻ የተፈፀመ ወይም የሚፀና ስለመሆኑ ክርክር የተነሳ እንደሆነ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን የሚኖረው ፍርድ ቤት ብቻ ነው፡፡

አንቀጽ ፩፻፲፮ ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር

በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት ስለመኖሩ ክርክር የተነሳ እንደሆነ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ስልጣን የሚኖረው ፍርድ ቤት ብቻ ነው፡፡

አንቀጽ ፩፻፲፯ ስለፍቺና ስለ ፍቺ ውጤቶች

ፍቺን የመወሰን ወይም በዚህ ሕግ አንቀጽ ፹፫ በተደነገገው መሠረት የፍቺ ውጤቶችን በተመለከተ ውሳኔ የመስጠት ወይም የማጽደቅ ሥልጣን የፍርድ ቤት ብቻ ነው፡፡

BACK



አንቀጽ ፩፻፲፰ በጋብቻ ውስጥ ስለሚፈጠሩ አለመግባባቶች

፩· በዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፲፯ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በጋብቻ ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶች ባልና ሚስቱ በሚመርጧቸው ሽማግሌዎች አማካይነት ይወሰናሉ።

፪· ሽማግሌዎቹ በሚሰጡት ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቤቱታ ለማቅረብ ይችላል።

፫· ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን ቅሬታ መርምሮ በሽማግሌዎቹ የተሰጠውን ውሳኔ ሊያፀና ፡ ሊያሻሽል ወይም ሊሽር ይችላል፤ የሚሰጠውም ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

ክፍል ፫

ስለ ዕርቅ

አንቀጽ ፩፻፲፱ አስታራቂ ሽማግሌዎችን ስለመምረጥ

፩· በዚህ ሕግ አንቀጽ ፹፪(፪) መሠረት ባልና ሚስት ጉዳያቸውን በዕርቅ ለመጨረስ በወሰኑ ጊዜ፣ አመቺ ሆኖ በሚያገኙት መንገድ አንድ ወይም ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ ሽማግሌዎችን በመምረጥ፣ ሽማግሌ እንዲመርጡ ከተነገራቸው ቀን አንስቶ በ፲፭ ቀናት ውስጥ የሽማግሌዎቹን ስም ዝርዝር ለፍርድ ቤቱ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል።

፪· ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሽማግሌዎች ስም ዝርዝር ሲቀርብለት ወይም ሽማግሌዎቹ እንደቀረቡ ወዲያውኑ መዝግቦ ዕርቅ የሚከናወንበትን የመፍትሔ አቅጣጫ የሚጠቁም ምክርና መመሪያ በመስጠት ወይም እንዲደርሳቸው በማድረግ የዕርቁ ወይም የዕርቁ ሙከራ ውጤት በሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ እንዲቀርብለት ያዛል።

፫· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ ቢኖርም፣ ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የዕርቁ ሂደት የደረሰበትን ደረጃ በየጊዜው ለመመርመርና ወቅታዊ ሪፖርት እንዲቀርብለት ማዘዝ ይችላል።

<u>አንቀጽ ፩፻፳ ስለተጨማሪ ጊዜ</u>

ከዕርቅ ሙከራው ሂደት አኳያ ባልና ሚስት ያለመግባባታቸውን በዕርቅ ሊጨርሱ ይችላሉ የሚል ግምት ያለው እንደሆነ፣ ፍርድ ቤቱ በዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፲፱ በተመለከተው ጊዜ ሳይገደብ ከአንድ ወር ያልበለጠ ተጨማሪ ጊዜ በመስጠት የዕርቅ ሙከራው እንዲቀጥል ሊያዝ ይችላል።

<u>አንቀጽ ፩፻፳፩ የአስታራቂ ሽማግሌዎች ኃላፊነት</u>

፩· አስታራቂ ሽማግሌዎች ባልና ሚስቱ የመፋታት ሃሳባቸውን እንዲተዉና ጉዳያቸውን በመግባባት እንዲጨርሱ ለማድረግ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ አለባቸው።

፪· አስታራቂ ሽማግሌዎቹ ጉዳዩ ከፍቺ በመለስ ሊፈታ እንደማ ይችል የተረዱ እንደሆነ ፣ ተጨማሪ ጊዜ ሳያስፈልጋቸው ስለደረሱበት ውጤት ለፍርድ ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ አለባቸው።

፫· አስታራቂ ሽማግሌዎች ጉዳዩን ከፍቺ በመለስ በማግባባት ለመፍታት ከመጣር አልፈው ባልና ሚስቱን የሚመለከት ማናቸውንም ትዕዛዝም ሆነ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን አይኖራ ቸውም።

<u>አንቀጽ ፩፻፳፪ የሪፖርት አለመቅረብ</u>

፩· በዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፲፱ እና ፩፻፳፩ መሠረት አስታራቂዎቹ ሪፖርት ሳያቀርቡ የቀሩ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ይዘጋዋል።

፪· መዝገቡ በተዘጋ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ባልና ሚስቱ ወይም ከሁለቱ አንዳቸው ጉዳያቸውን በዕርቅ አለመጨረሳቸውንና ሪፖርቱ በወቅቱ ያልቀረበበትን ምክንያት በመግለጽ ጉዳያቸው እንዲንቀሳቀስላቸው የጠየቁ እንደሆነ፣ ፍርድ ቤቱ ጥያቄያቸው ተገቢ ሆኖ ካገኘው መዝገቡን በመክፈት በሕጉ መሠረት የራሱን ውሳኔ ይሰጣል።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚሰጠው

BACK



መዝገቡን የመዝጋት ውሳኔ፡ ባልና ሚስቱ ወይም ከሁለቱ አንዳቸው አዲስ አቤቱታ በማቅረብ ጉዳያቸው እንዲታይላቸው ከመጠየቅ የሚያግዳቸው አይሆንም።

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## ስለመወለድ

## ክፍል ፩

## አባትነትንና እናትነትን ስለማወቅ

### ንዑስ ክፍል ፩

### አጠቃላይ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ ፩፻፳፬ የሕጉ ድንጋጌዎች አስገዳጅ ስለመሆናቸው**

ሕጉ በግልጽ የሚፈቅድ ካልሆነ በስተቀር፡ አባትነትና እናትነትን ስለማወቅ የተመለከቱት የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች በስምምነት ሊለወጡ አይችሉም።

**አንቀጽ ፩፻፳፭ ስለእናትነት**

እናት የተባለችው ሴት ልጁን የወለደችው በመሆንዋ ብቻ እናትነቷ ይታወቃል።

**አንቀጽ ፩፻፳፮ ስለአባትነት**

፩· ልጅ በሚፀነስበት ወይም በሚወላድበት ጊዜ በእናትየዋና በአንድ ወንድ መካከል በሕግ የታወቀ ግንኙነት መኖሩ በመረጋገጡ ምክንያት አባትነት ይታወቃል።
፪· አባትየው ልጁን ልጄ ነው ሲል በመቀበሉ ምክንያትም አባትነት ሊታወቅ ይችላል።
፫· በፍርድ ቤት በሚሰጥ ውሳኔም አባትነት እንዲታወቅ ሊደረግ ይችላል።

### ንዑስ ክፍል ፪

### አባትነት በሕግ ግምት የሚታወቅ ስለመሆኑ

**አንቀጽ ፩፻፳፯ ባል አባት ነው ተብሎ የሚገመት ስለመሆኑ**

በጋብቻ ውስጥ የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ አባቱ ነው የሚባለው ባልየው ነው።

**አንቀጽ ፩፻፳፰ የግምቱ አጠቃላይነት**

፩· ከልጁ ጋር ያለው የእናት ግንኙነት በየትኛውም ዘዴ የተረጋገጠ

BACK



ቢሆንም ፡ በአንቀፅ ፩፻፷፮ የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

፪· የልጁ የልደት ምስክር ወረቀት ባልየው አባት ያለመሆኑን ወይም የልጁ አባት ሌላ ሰው መሆኑን የሚያመለክት ቢሆንም እንኳን፡ ይኸው ድንጋጌ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

፫· ከዚህ በላይ የተመለከተው ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ የልደት ምስክር ወረቀቱ እንዲታረም ይደረጋል።

አንቀጽ ፩፻፷፰ እርግዝናው ስለሚቀይበት ጊዜ

፩ ጋብቻው ከተፈፀመ ከ፩፻፹ ቀናት በኋላ ወይም ጋብቻው በፈረሰ በ፫፻ ቀናት ውስጥ የተወለደ እንደሆነ ፡ ልጁ በጋብቻው ውስጥ እንደተፀነሰ ይቆጠራል።

፪· ለዚህ ተቃራኒ የሆነ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም።

አንቀጽ ፩፻፷፱ የባልየው መጥፋት

በዚህ ሕግ ስለአባትነት የተደነገጉት የሕግ ግምቶች በሕግ አባት ነው የሚባለው ሰው መጥፋቱ በተነገረበት ፍርድ ላይ ስለመኖሩ ወሬ የተሰማበት የመጨረሻ ቀን ነው ከተባለበት ከ፫፻ ቀናት በኋላ ለተወለደ ልጅ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

አንቀጽ ፩፻፸ ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር

፩· ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብረው በሚኖሩበት ጊዜ የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ አባት በዚሁ ግንኙነት ከእናትየዋ ጋር አብሮ የሚኖረው ሰው ነው።

፪· በዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፷፯ እና ፩፻፷፰ ስለግምቱ አጠቃላይነትና እርግዝናው ስለሚቀይበት ጊዜ የተመለከቱት ድንጋጌዎች በዚህ አንቀጽ ለተመለከተው የሕግ ግምትም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

## ንዑስ ክፍል ፫
## ልጅነትን ስለመቀበል

አንቀጽ ፩፻፸፩ (፩) መሠረቱ

ከዚህ በላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት የልጁ አባት ሊታወቅ ያልቻለ እንደሆነ ፡ አባትየው ልጄ ነው ሲል በመቀበሉ

BACK



ሊታወቅ ይችላል።

አንቀጽ ፩፻፴፪ (፪) ትርጓሜ

አንድ ሰው፣ አንድን የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ የእርሱ ልጅ መሆኑን አምኖ በመቀበል ቃሉን የሰጠ እንደሆነ የልጁ አባት መሆኑን ተቀበለ ይባላል።

አንቀጽ ፩፻፴፫ (፫) ሥርዓት (ፎርም)

አንድ ሰው የክብር መዝገብ ሹም ፊት በመቅረብ አባት መሆኑን በመግለፅ በሚሰጠው ቃል ወይም በጽሑፍ በሚያደርገው ኑዛዜ ወይም በሌላ በማናቸውም ሥልጣን በተሰጠው ባለሥልጣን በተረጋገጠ ሰነድ አማካይነት አባት መሆኑን በመግለፅ ልጅነትን ለመቀበል ይችላል።

አንቀጽ ፩፻፴፬ ስለወኪልነት

፩· አካለ መጠን ያልደረሰ ቢሆንም እንኳን ልጄ ነው ሲል ቃል ለመስጠት የሚችለው አባት ብቻ ነው።

፪· ቃሉን ሌላ ሰው እንዲሰጥለት ማድረግ የሚችለው በፍርድ ቤት የፀደቀ ልዩ የውክልና ሥልጣን በመስጠት ብቻ ይሆናል።

፫· በፍርድ የተከለከለ ሰው ቃሉን በራሱ ወይም ፍርድ ቤት ሲፈቅድ በእርሱ ስም በሕጋዊ ወኪሉ አማካይነት ሊሰጥ ይችላል።

አንቀጽ ፩፻፴፭ የአባትየው መሞት

የልጁ አባት የሞተ ወይም ፈቃዱን ለመስጠት የማይችል በሆነ ጊዜ፣ ከአባትየው ወላጆች አንዱ በእርሱ ስም ልጁን ሊቀበል ይችላል።

አንቀጽ ፩፻፴፮ እናት የተቀባዩን አባትነት ስላለማመንዋ

፩· የልጁ እናት የተቀባዩን አባትነት እውነትነት ያለው መሆኑን ካላመነች በስተቀር አባት ልጄ ነው ሲል የሚሰጠው ቃል በሕግ ፊት ውጤት አይኖረውም።

፪· የልጁ እናት የሞተች ወይም ፈቃድዋን ለመግለጽ የማትችል ሆና የተገኘች እንደሆነ፣ የእምነት ቃሉ ከልጁ እናት ወላጆች በአንደኛው ሊሰጥ ይችላል።

፫· የልጁ እናት ወላጆች በሌሉ ጊዜ፣ ወደላይ በሚቆጠር ሌላ ወላጅ፣

BACK



ወይም በፍርድ በተከለከለው ሰው አሳዳሪ ሊሰጥ ይችላል።

አንቀጽ ፩፻፴፯ ስለ ልጁ ለአካለ መጠን መድረስ

ልጅነትን የመቀበሉ ተግባር የተከናወነው ልጁ አካለ መጠን ከደረሰ በኋላ የሆነ እንደሆነ አባት ልጁን መቀበሉ ውጤት የሚያገኘው ልጁ አባትነቱን የተቀበለ እንደሆነ ነው።

አንቀጽ ፩፻፴፰ እምኖ የመቀበሉ ሁኔታ

በዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፴፮ እና ፩፻፴፯ የተመለከቱት ሰዎች፣ የመቀበሉ ድርጊት መከናወኑን ካወቁበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ክርክር ያላነሱ እንደሆነ አምነው እንደተቀበሉ ይቆጠራል።

አንቀጽ ፩፻፴፱ የልጁ መሞት

ልጅየው ወደ ታች የሚቆጠሩ ተወላጆችን ተክቶ ካልሞተ በስተቀር ፣ ልጅነቱን አውቆ መቀበል አይቻልም።

አንቀጽ ፩፻፵ ቃልን ስለመሻር

፩· ልጄ ነው ሲል አባት የሰጠውን ቃል መሻር አይችልም።

፪· አሳዳሪው አስቀድሞ ስምምነቱን ካልሰጠ በስተቀር ፣ ልጅነትን የተቀበለ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ አካለ መጠን ከመድረሱ በፊት እና አካለ መጠን ከደረሰ በኋላም እስከ አንድ ዓመት ጊዜ ድረስ ልጄ ነው ሲል የሰጠውን ቃል ሊሽር ይችላል።

፫· ልጄ ነው ሲል የተቀበለበትን ቃሉን ለመሻር ብቸኛ መብት ያለው አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ብቻ ነው። የልጁ ሕጋዊ ወኪሎችም ሆኑ ወራሾቹ በዚህ መብት መጠቀም አይችሉም።

አንቀጽ ፩፻፵፩ ስለማፍረስ

፩· ልጅነትን ለመቀበል፤ የተነገረ ቃል በኃይል የተሰጠ መሆኑን በማስረዳት ሊፈርስ ይችላል።

፪· ልጄ ነው ብሎ ከተቀበለው ሰው ሊፀነስ የማይችል ለመሆኑ በማያሻማ አኳኋን ካልተረጋገጠ በስተቀር ፣ ልጅነትን የመቀበሉ ድርጊት በስህተት ወይም በማታለል የተደረገ ነው በማለት ሊፈርስ አይችልም።

አንቀጽ ፩፻፵፪ አንድን ልጅ ብዙ አባቶች ሊቀበሉት ስላለመቻላቸው

ቀደም ሲል የተሰጠ ልጅነትን የመቀበል ቃል እንዲፈርስ ካልተደረገ

BACK



በስተቀር ፡ ሌላ ሰው ልጁ ነው ሲል የሚሰጠው ቃል ተቀባይነት አይኖረውም።

## ንዑስ ክፍል ፬
## በፍርድ ቤት ውሳኔ አባትነት እንዲታወቅ ስለማድረግ

### አንቀጽ ፩፻፵፫ (፩) በፍርድ ስለሚነገር አባትነት

ከዚህ በላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት የልጁ አባት ያልታወቀ ወይም የተካደ እንደሆነና ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲሟሉ አባትነት በፍርድ ውሳኔ ሊታወቅ ይችላል፡

ሀ) ልጁ በተፀነሰበት ጊዜ በእናቲቱ ላይ የመድፈር ወይም የመጠለፍ ተግባር የተፈፀመባት ሲሆን፡

ለ) ሆን ተብሎ በተደረገ የተንኮል ድርጊት ፡ ሥልጣንን ያለአግባብ በመጠቀም፡ አገባሻለሁ ሲል የተሰፋ ቃል በመስጠት ወይም በሌላ ተመሳሳይ መንገድ ልጁ በተፀነሰበት ጊዜ በእናቲቱ ላይ የማሳት ተግባር የተፈፀመባት ሲሆን፡

ሐ) አባት ነው በተባለው ሰው የተጻፉና በማያሻማ ሁኔታ አባት ነቱን የሚያረጋግጡ ደብዳቤዎች ወይም ሌሎች ጽሑፎች ሲኖሩ፡

መ) በሕግ የታወቀ ግንኙነት ሳይኖራቸው፡ የልጁ እናትና አባት የተባለው ሰው በህግ በተመለከተው የእርግዝና ጊዜ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በግብረ ሥጋ ግንኙነት አብረው የኖሩ እንደሆነ፡

ሠ) አባት ነው የተባለው ሰው ልጁን በመንከባከብ ወይም በማስ ተማር ወይም በማሳደጉ ላይ እንደአባት በመሆን የተሳተፈ እንደሆነ።

### አንቀጽ ፩፻፵፬ (፪) አባትነትን በፍርድ ለማረጋገጥ ስለሚቀርብ ክስ

ከዚህ በላይ በተመለከተው አኳኋን አባትነት በፍርድ እንዲነገር የሚ ቀርብ ክስ ፡ ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች ባሉ ጊዜ ተቀባይነት አይኖረውም፡

ሀ) ሌላኛው ሰው የልጁ አባት ላለመሆኑ በደም ምርመራ ወይም በሌላ አስተማማኝ የህክምና ዘዴ ካልተረጋገጠ በስተቀር በሕግ

በተወሰነው የእርግዝና ጊዜ ውስጥ እናቲቱ ከሌላ ሰው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈፀምዋ የተረጋገጠ እንደሆነ፡

ለ) አባት ነው የተባለው ሰው በህግ በተወሰነው የእርግዝና ጊዜ ውስጥ በመጥፋቱ፡ ወይም በአደጋ ምክንያት አባት ሊሆን የማይችልበትን ሁኔታ ሲያረጋግጥ፤

ሐ) አባት ነው የተባለው ሰው በደም ምርመራ ወይም በሌላ አስተማማኝ የህክምና ዘዴ የልጁ አባት ሊሆን የማይችል መሆኑን ሲያረጋግጥ።

## አንቀጽ ፩፻፷፰ ሌላ ሁኔታ ስላለመኖሩ

በዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፷፯ ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውጪ አባትነት በፍርድ ቤት ውሳኔ ሊታወቅ አይችልም።

## ክፍል ፪

## አባትነትን በመወሰን ላይ ስለሚኖረው የሕግ ግጭት

## አንቀጽ ፩፻፷፱ አባትነትን ስለመወሰን (፩) መሠረቱ

ከዚህ በላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ተፈጻሚ በማድረግ አንድ ልጅ ከአንድ በላይ አባቶች አሉት ከተባለ የልጁ አባትነት በህግ በሚሰጣቸው ሰዎች መካከል በሚደረግ ስምምነት ሊወሰን ይችላል።

## አንቀጽ ፩፻፸ (፪) ሥርዓት (ፎርም)

፩· የአባትነት ውሳኔ የሚያሰጠውን ስምምነት ሶስት ምስክሮች ሊያረጋግጡትና ፍርድ ቤት ሊያጸድቀው ይገባል።

፪· ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካላጋጠመ በስተቀር የልጁን እናት ቃል መስማት ይገባል።

## አንቀጽ ፩፻፸፩ የሕግ ግምት

ስለአባትነት በሚደረገው ክርክር ስምምነት ያልተገኘ እንደሆነና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ከዚህ ቀጥለው ያሉትን ሁለት የህግ ግምቶች በመከተል ይፈጸማል፡

ሀ) ጋብቻ ሳይፈጸም እንደ ባል ከሚኖር ሰው ይልቅ፣ ህጋዊው ባል ይመረጣል።

ለ) ልጁ በተፀነሰበት ጊዜ ከነበረው ባል ወይም ከሴትየዋ ጋር አብሮ

ይኖር ከነበረው ሰው ይልቅ እናቲቱ ልጁን ስትወልድ የነበራት ባል ወይም አብሮ የሚኖር ሰው የልጁ አባት ነው ማለት ይገባል።

**አንቀጽ ፩፻፵፱ (፩) አባትነትን በስምምነት ስለማስተላለፍ**

፩· ልጁ የተወለደው ጋብቻው ከተፈጸመ ወይም ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ከተጀመረ አንስቶ በ፪፻፲ ቀናት ውስጥ የሆነ እንደሆነ ባልየው ወይም ከሴትየዋ ጋር እንደባል አብሮ የሚኖረው ሰው የልጁ አባት እኔ ነኝ ለሚል ሌላ ሰው በስምምነት አባትነቱን ሊያስተላልፍለት ይችላል።

፪· እንዲሁም ልጁ ከጋብቻው መፍረስ ወይም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖሩ ከተቋረጠበት ቀን በኋላ ፪፻፲ ቀኖችን አሳልፎ ተወልዶ እንደሆነ ባልየው ወይም እንደባል አብሮ የኖረው ሰው ከዚህ በላይ የተነገረው መብት ይኖረዋል።

**አንቀጽ ፩፻፶ (፪) ሥርዓት (ፎርም)**

፩· በስምምነት የሚደረግ አባትነትን የማስተላለፍ ድርጊት ሶስት ምስክሮች ሊያረጋግጡትና ፍርድ ቤት ሊያጸድቀው ይገባል።

፪· ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካላጋጠመ በስተቀር የእናቲቱ ቃል መሰማት አለበት።

**አንቀጽ ፩፻፶፩ ስለወኪልነት**

፩· በዚህ ክፍል የተመለከቱትን ስምምነቶች አካለ መጠን የደረሱና በፍርድ ያልተከለከሉ ባለጉዳዮች ራሳቸው መጨረስ አለባቸው።

፪· ስምምነቱን ሌላ ሰው እንዲያከናውንለት ማድረግ የሚቻለው፣ በፍርድ ቤት የፀደቀ ልዩ የውክልና ሥልጣን በመስጠት ብቻ ይሆናል።

**አንቀጽ ፩፻፶፪ ቃልን ስለመሻር**

አባትነትን በስምምነት የመወሰን ወይም የማስተላለፍ ድርጊት ሊሻር አይችልም።

**አንቀጽ ፩፻፶፫ ስለማፍረስ**

፩· ልጅነትን ለመቀበል የተደረገ ስምምነት በኃይል ድርጊት የተሰጠ መሆኑን በማስረዳት ሊፈርስ ይችላል።

BACK



፪· ልጁ ነው ብሎ ከተቀበለው ሰው ሊፀነስ የማይችል ለመሆኑ በማያሻማ አኳኋን ካልተረጋገጠ በስተቀር፣ ልጅነትን የመቀበሉ ስምምነት በስህተት ወይም በማታለል የተደረገ ነው በማለት ሊፈርስ አይችልም።

## ክፍል ፫
## ስለ ልጅነት ማስረጃ

**አንቀጽ ፩፻፶፬ የልደት ምስክር ወረቀት**

በአባትነት ወይም በእናትነት በኩል የአንድ ሰው ልጅነት፣ የእገሌ ልጅ ነው የሚል የልደት ምስክር ወረቀት በማቅረብ ይረጋገጣል ።

**አንቀጽ ፩፻፶፭ የልደት ምስክር ወረቀት በሌለ ጊዜ ስለማቀርብ ማስረጃ**

የልደት ምስክር ወረቀት የሌለ እንደሆነ የልጅነት ሁኔታ በመኖሩ ልጅነት ይረጋገጣል ።

**አንቀጽ ፩፻፶፮ የልጅነት ሁኔታ መኖር (፩) ትርጓሜ**

አንድ ሰው የልጅነት ሁኔታ አለው የሚባለው በማኅበረሰቡ ዘንድ የእርሱ ወይም የእርሷ ልጅ ነው እየተባለ የሚገመት ሲሆን ነው ።

**አንቀጽ ፩፻፶፯ ልጅነትን በልጅነት ሁኔታ ስለማስረዳት**

፩· ከዚህ በላይ በተመለከተው አንቀጽ መሠረት የልጅነት ሁኔታ መኖሩን ለማስረዳት የተቻለ እንደሆነ ፣ ፍርድ ቤቱ ልጁ ነው ሲል የህግ ግምት ይወስዳል ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን ግምት፣ ልጁ፣ የተባለው ሰው ልጅ ሊሆን እንደማይችል በማስረዳት ማፍረስ ይቻላል ።

**አንቀጽ ፩፻፶፰ ተወላጅነትን ለማስረዳት ስለሚቀርብ ክስ**

፩· የልጅነት ሁኔታ የሌለ እንደሆነ ተወላጅነትን በምስክሮች ወይም ማናቸውንም ዓይነት ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት ይቻላል።

፪· ተ ላጅነትን የማረጋገጥ ክስ ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተቀር

ሊቀርብ አይችልም ።

፫· ተወላጅነትን ለማረጋገጥ ለሚቀርበው ክስ ፈቃድ የሚሰጠው፣ ፍርድ ቤቱ ክሱን እንዲቀበል የሚያደርጉ ተጨባጭነት ካላቸው ተግባራት የሚመነጩ ግምቶች ወይም ምልክቶች ሲኖሩ ብቻ ነው ።

## አንቀጽ ፩፻፷፱ ክስን ስላለመቀበል

ተወላጅነቱን ለማረጋገጥ የሚፈልገው ሰው ስለመወለዱ ከተሰጠው የልደት ምስክር ወረቀት ጋር የሚስማማ የልጅነት ሁኔታ ያለው እንደሆን ከሌላ ሰው ተወላጅነቱን ለማረጋገጥ ክስ ለማቅረብ አይፈቀድለትም ።

## አንቀጽ ፩፻፸ ስለ ከሳሽ

፩· ተወላጅነትን ለማረጋገጥ ክስ ለማቅረብ የሚችሉት ልጁ ወይም አሳዳሪው ወይም ወራሾቹ ናቸው ።

፪· እንደዚሁም የልጁ አባት ወይም እናት ነን የሚሉት ሰዎች ክስ ለማቅረብ ይችላሉ ።

## አንቀጽ ፩፻፸፩ ክስ ስለሚቀርብበት ጊዜ

፩· ልጁ በህይወት እስካለ ድረስ ተወላጅነቱን ለማረጋገጥ ክስ ለማቅረብ ይችላል ።

፪· የልጁ ወላጆች ወይም አሳዳሪዎች ልጁ አካለመጠን ባልደረሰበት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር ክስ ለማቅረብ አይችሉም።

፫· ልጁ ሃያ ዓመት ሳይሞላው የሞተ እንደሆነ እርሱ ከሞተ በኋላ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልሆነ በስተቀር ወራሾቹ ክስ ለማቅረብ አይችሉም።

## አንቀጽ ፩፻፸፪ ስለ ተከሳሽ

፩· ተወላጅነትን ለማረጋገጥ ክሱን ያቀረበችው እናት ነኝ የምትል ሴት በሆነች ጊዜ ክሱ የሚቀርበው በልጁ ላይ ነው ።

፪· ሆኖም ክሱ የቀረበው በሌላ ሰው ሲሆን ክሱ የሚቀርበው እናት ነች በተባለችው ወይም በወራሾችዋ ላይ ነው ።

## ክፍል ፬
## በተወላጅነት ላይ ስለሚነሳ ክርክርና ስለ መካድ

### ንዑስ ክፍል ፩
### በተወላጅነት ላይ ስለሚነሳ ክርክር

**አንቀጽ ፩፻፷፫ መሠረቱ**

በእናት በኩል ያለው ተወላጅነት በማንኛውም ባለጉዳይ በማንኛውም ጊዜ ሁሉ ክርክር ሊደረግበት ይችላል ።

**አንቀጽ ፩፻፷፬ ክስን ስለመቀበል**

፩· በተወላጅነት ላይ ስለሚደረገው ክርክር የሚቀርበው ክስ ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተቀር ሊቀርብ አይችልም።

፪· በተወላጅነት ላይ ክርክር ለማድረግ ለሚቀርበው ክስ ፈቃድ የሚሰጠው፣ ፍርድ ቤቱ ክሱን እንዲቀበል የሚያደርጉት ተጨባጭነት ካላቸው ተግባራት የሚመነጩ ግምቶች ወይም ምልክቶች ሲኖሩ ብቻ ነው ።

**አንቀጽ ፩፻፷፭ ክስን ስላለመቀበል**

ልጁ ተወላጅነቱን የሚያረጋግጥ የልደት ምስክር ወረቀትና ከዚህ ጋር የሚስማማ የልጅነት ሁኔታ ያለው እንደሆነ በተወላጅነቱ ላይ ለመከራከር ፈቃድ አይሰጥም ።

**አንቀጽ ፩፻፷፮ ስለ ተከሳሽ**

፩· በተወላጅነት ምክንያት የሚቀርበው ክስ በተወላጅነቱ ላይ ክርክር በተነሳበት ሰው ላይ ወይም በወራሾቹ ላይ ይመሰረታል።

፪· የልጁን እናት፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም የልጁን አባት፣ ክርክሩ ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

### ንዑስ ክፍል ፪
### ስለ መካድ

**አንቀጽ ፩፻፷፯ መሠረቱ**

በአባት በኩል ያለን መወለድ መቃወም የሚቻለው የመካድ ክስ በማቅረብ ብቻ ነው ።

**አንቀጽ ፩፻፷፰ ከልጁ እናት ጋር የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ስላለመኖር**

**(፩) መሠረቱ**

የልጁ አባት ነህ ተብሎ በህግ አባትነት የሚሰጠው ሰው ልጁ ከመወለዱ በፊት በ፫፻ኛውና በ፩፻፹ኛው ቀናት መካከል ባለው ጊዜ

ውስጥ ከልጁ እናት ጋር የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ላለመፈፀሙ በማያጠራጥር ሁኔታ ያስረዳ እንደሆነ የተባለውን ልጅ ልጄ አይደለም ለማለት ይችላል ።

**አንቀጽ ፩፻፸፱ (፪) የሕግ ግምት**

፩· ከሁለቱ አንዱ ባቀረበው የመፋታት ጥያቄ መሠረት ወይም በሁለቱ መካከል በተደረገው የመለያየት ስምምነት ምክንያት ባልና ሚስቱ በእውነት ተለያይተው በነበሩበት ጊዜ በመካከላቸው የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት እንዳልተደረገ ይገመታል ።

፪· ለዚህ ተቃራኒ ሆኖ የሚቀርበው ማስረጃ በማናቸውም ምክንያቶች ቢሆን ይሰማል ።

**አንቀጽ ፩፻፹ አባት ለመሆን ስለአለመቻሉ (፩) መሠረቱ**

በሕግ የልጁ አባት ነህ የተባለው ሰው የዚሁ ልጅ አባት ሊሆን አለመቻሉን በማያጠራጥር አኳኋን በማስረዳት ለመካድ ይችላል ።

**አንቀጽ ፩፻፹፩ (፪) ክስን ለመቀበል ስለመቻል**

፩· ከዚህ በላይ በተመለከተው አንቀጽ መሠረት የሚቀርበው የመካድ ክስ ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተቀር ሊቀርብ አይችልም።

፪· ፈቃዱም የሚሰጠው ፍርድ ቤት ክሱን እንዲቀበል የሚያደርገው በቂና አስተማማኝ ከሆነ መረጃ የሚመነጭ የህሊና ግምት ወይም ከባድ ምልክት ሲኖር ብቻ ነው።

**አንቀጽ ፩፻፹፪ (፫) ስለ ህሊና ግምቶችና ከባድ ምልክቶች**

፩· የህሊና ግምቶችና ከባድ ምልክቶች የሚባሉት ልጅህ ነው ከተባለው ሰው አባትነት ጋር የማይስማሙ ለመሆናቸው በሳይንስ እውቀት ተለይተው የሚታዩ ተጨባጭ መረጃዎች ሊሆኑ ይችላሉ ።

፪· እንዲሁም እነዚህ ነገሮች ሴቲቱ በሰውየው አባትነት ላይ ጥርጣሬ በሚያሳድር አኳኋን የልጁን መወለድ ወይም እርግዝናዋን ከሰውየው ከደበቀችበት ድርጊት ሊመነጩ ይችላሉ ።

**አንቀጽ ፩፻፹፫ (፬) ስለ ሴሰኝነት (በባል ላይ ስለሚደረግ ዝሙት) ወይም ስለ እናቲቱ ማመን**

እናቲቱ በባልዋ ላይ ያደረገችው የሴሰኝነት (የዝሙት) ሥራ ወይም ልጁ የሌላ ሰው ለመሆኑ የምትሰጠው የእምነት ቃል ብቻ እንደ ከባድ

BACK



ምክንያት ሊቆጠሩ አይችሉም ።

**አንቀጽ ፩፻፸፬ ስለ ከሳሽ**

፩· የእኔ ልጅ አይደለም ብሎ የመካድ ክስ ለማቅረብ የሚችለው የልጁ አባት ነህ ተብሎ በህግ ግምት የሚሰጠው ሰው ብቻ ነው።

፪· በዚህ ጉዳይ በተለይ እናቲቱ ፡ አባት ነኝ ባዩ ፡ ዐቃቢ ሕግ ወይም ልጁ ራሱ ክስ ሊያቀርቡ አይችሉም ።

**አንቀጽ ፩፻፸፭ በፍርድ የተከለከለ ሰው**

፩· በፍርድ የተከለከለ ሰው ፍርድ ቤትን አስፈቅዶ የመካድ ክስ ለማቅረብ ይችላል ።

፪· እንዲሁም በፍርድ የተከለከለው ሰው አሳዳሪ ይህንኑ የፍርድ ቤት ፈቃድ ከተቀበለ በኋላ በፍርድ በተከለከለው ሰው ስም ሆኖ የመካድ ክስ ለማቅረብ ይችላል ።

**አንቀጽ ፩፻፸፮ ክስ ስለሚቀርብበት ጊዜ (፩) መሠረቱ**

፩· የእኔ ልጅ አይደለም የሚል የመካድ ክስ የልጁን መወለድ ካወቀበት ወይም ማወቅ ከሚገባው ቀን ጀምሮ በ፩፻፹ ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት ።

፪· እናትነት የተወሰነው ተወላጅነትን ለማረጋገጥ በቀረበ ክስ ሲሆን የመካድ ክስ የሚቀርበው ተወላጅነትን ለማረጋገጥ የቀረበውን ክስ የሚወስን የመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠ ጀምሮ ባሉት ፩፻፹ ቀናት ውስጥ ነው ።

**አንቀጽ ፩፻፸፯ (፪) ልዩ ሁኔታ**

፩· በሕግ ግምት የልጁ አባት ነህ የሚባለው ሰው የሞተ ወይም የመካድ ክስ ለማቅረብ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ችሎታውን ያጣ እንደሆነ ከተወላጆቹ አንዱ በርሱ ፋንታ ሆኖ የመካድ ክስ ሊያቀርብ ይችላል ።

፪· ተወላጆቹ የሌሉ እንደሆነ አባትና እናቱ፡ እነዚህም የሌሉ እንደሆነ ወደ ላይ ከሚቆጠሩ ወላጆቹ አንዱ መብቱን ሊሰራበት ይችላል ።

፫· ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች የሌሉ እንደሆነ ፡ የተባለውን መብት ማንኛውንም ሌላ ወራሽ ወይም ወኪልን ሳይጨምር ፡ ከወንድሞቹ ወይም ከእህቶቹ አንዱ ሊሰራበት ይችላል ።

BACK



**አንቀጽ ፩፻፸፯ ክስን ስላለመቀበል**

ባልየው በጽሁፍ በሰጠው ፈቃድ መሠረት ልጁ በሰው ሰራሽ ዘዴ የተፀነሰ ለመሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ የመካድ ክስ ለማቅረብ የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም ።

**አንቀጽ ፩፻፸፰ ስለ ተከሳሾች**

፩· የመካድ ክስ በልጁ ላይ፣ እርሱም ሞቶ እንደሆነ በወራሾቹ ላይ ይቀርባል ።

፪· የልጁን እናት በሚቀርበው ክስ ውስጥ እንድትገባ ማድረግ ያስፈልጋል ።

፫· ልጁ አካለመጠን ያልደረሰ ከሆነ ፍርድ ቤት በተለይ ለዚህ ጉዳይ የመረጠው ሞግዚት ወኪል ይሆነዋል ።

## ምዕራፍ አሥር

## ስለ ጉዲፈቻ

**አንቀጽ ፩፻፹ ስለጉዲፈቻ ዝምድና (፩) መሠረቱ**

በአንድ ሰውና በአንድ ልጅ መካከል በሚደረግ ስምምነት የጉዲፈቻ ዝምድና ሊፈጠር ይችላል ።

**አንቀጽ ፩፻፹፩ (፪) ውጤቱ**

በዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፹፪ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የጉዲፈቻ ልጅ በማናቸውም ረገድ ቢሆን እንደ ጉዲፈቻ አድራጊው ልጅ ይቆጠራል።

**አንቀጽ ፩፻፹፪ (፫) ልዩ ሁኔታ**

፩· ጉዲፈቻ፣ የጉዲፈቻውን ስምምነት በግልጽ የተቃወሙትን ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆችን ወይም ወደጎን የሚቆጠሩ ዘመዶችን በሚመለከት ውጤት አይኖረውም።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ተቃውሞ፣ ስምምነቱ በፍርድ ቤት መጽደቁ በታወቀ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በፍርድ ቤት መዝገብ ካልተመዘገበ በስተቀር አይፀናም።

**አንቀጽ ፩፻፹፫ የጉዲፈቻ ልጅ ከቀደምት ቤተሰቦቹ ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት**

፩· የጉዲፈቻ ልጅ ከቀደምት ቤተሰቦቹ ጋር ያለው የዝምድና

BACK



ግንኙነት እንደተጠበቀ ይቆያል።

፪· የጉዲፈቻ ልጅየው ሚስት/ባል እና ተወላጆችም ከቀደምት ቤተሰቦቹ ጋር የዝምድና ግንኙነት ይኖራቸዋል።

፫· በቀደምት ቤተሰቦቹና በጉዲፈቻ ቤተሰቦቹ መካከል መምረጥ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ፡ ለጉዲፈቻ ቤተሰቦቹ ቅድሚያ ይሰጣል።

<u>አንቀጽ ፩፻፹፱ የጉዲፈቻ አድራጊው ዕድሜ</u>

፩· ዕድሜው ከ፳፭ ዓመት ያላነሰ ማንኛውም ሰው የጉዲፈቻ አድራጊ ሊሆን ይችላል።

፪· ጉዲፈቻ አድራጊዎች ባልና ሚስት በሆኑ ጊዜ ፡ የአንዳቸው ዕድሜ ፳፭ ዓመት የሞላ ከሆነ በቂ ነው።

<u>አንቀጽ ፩፻፺ የጉዲፈቻ ልጅ ዕድሜ</u>

ዕድሜው ከ፲፰ ዓመት በታች የሆነና ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ያልወጣ ማንኛውም ሰው የጉዲፈቻ ልጅ ለመሆን ይችላል።

<u>አንቀጽ ፩፻፺፩ ያገባ ሰው ስለሚያደርገው የጉዲፈቻ ስምምነት</u>

፩· ጉዲፈቻ አድራጊው ያገባ በሚሆንበት ጊዜ ፡ ባልና ሚስቱ በጋራ ልጁን የጉዲፈቻ ልጃቸው የሚያደርጉት ካልሆነ በስተቀር የጉዲፈቻ ስምምነት ለማድረግ አይቻልም።

፪· የጉዲፈቻው ልጅ፡ የጉዲፈቻ አድራጊው ባል ወይም ሚስት ልጅ በሆነ ጊዜ ፡ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

፫· እንዲሁም ፡ ከባል እና ከሚስት አንደኛው ፈቃዱን ለመስጠት የማይችል ሲሆን ተፈፃሚነት አይኖረውም።

<u>አንቀጽ ፩፻፺፪ የተፀነሰን ልጅ የጉዲፈቻ ልጅ ስለማድረግ</u>

፩· የተፀነሰን ልጅ የጉዲፈቻ ልጅ ማድረግ ይቻላል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ቢኖርም፡ ልጁ በተወለደ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ እናቲቱ ስምምነቱን በገዛ ፈቃድዋ ብቻ ለመሠረዝ ትችላለች።

<u>አንቀጽ ፩፻፺፫ ስለጉዲፈቻ አድራጊው ልጆች</u>

፩· ጉዲፈቻ አድራጊው ከአብራኩ የተገኙ ልጆች ያሉት መሆኑ የጉዲፈቻ ስምምነት ከማድረግ የሚያግደው አይሆንም ።

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ፡ ፍርድ ቤቱ የጉዲፈቻ ስምምነቱን ከማጽደቁ አስቀድሞ ጉዲፈቻ አድራጊው ከአብራኩ የተገኙ ልጆች ያሉት መሆኑ በጉዲፈቻ ልጁ መልካም አስተዳደግና ጥቅም ላይ ሊኖረው የሚችለውን ተፅዕኖ ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።

**አንቀጽ ፩፻፹፱ አንድ ልጅ ከአንድ በላይ ጉዲፈቻ አድራጊ ሊኖረው የማይችል ስለመሆኑ**

፩· ባልና ሚስት ካልሆኑ በስተቀር ማንኛውም ልጅ ለብዙ ሰዎች የጉዲፈቻ ልጅ ሊሆን አይችልም።

፪· ጉዲፈቻ አድራጊው የሞተ እንደሆነ ግን ፡ አዲስ የጉዲፈቻ ስምምነት ለማድረግ ይቻላል።

፫· ልጅየው የባልና ሚስት የጉዲፈቻ ልጅ ከሆነና ከባልና ሚስቱ አንደኛው የሞተ እንደሆነ ፡ በሕይወት ካለው ሰው ጋር የሚጋባው አዲስ ተጋቢ የጉዲፈቻ ልጅ ሊያደርገው ይችላል።

**አንቀጽ ፩፻፺ ስምምነቱን ስለሚያደርጉ ወገኖች**

የጉዲፈቻው ስምምነት በጉዲፈቻ አድራጊውና በልጁ አሳዳሪ መካከል ይደረጋል።

**አንቀጽ ፩፻፺፩ የጉዲፈቻው ልጅ ወላጆች ፈቃድ**

፩· የልጁ አባትና እናት በሕይወት ያሉና የታወቁ ከሆነ ልጁ የጉዲፈቻ ልጅ እንዲሆን ፈቃዳቸውን እንዲሰጡ ያስፈልጋል።

፪· ከወላጆቹ አንደኛው የሞተ ፡ የጠፋ ፡ የማይታወቅ እንደሆነ ወይም ፈቃዱን ለመስጠት የማይችል ሲሆን ሌላኛው ወላጅ ፈቃዱን ይሰጣል።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም፡ ከወላጆቹ አንዱ ፈቃዱን ለመስጠት ያልፈለገ እንደሆነና የልጁ ዕድሜ ፲ ዓመትና ከዚያ በላይ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ያንደኛውን ወላጅ ፈቃድና የልጁን አስተያየት በመጠየቅ ጉዲፈቻውን ሊያፀድቀው ይችላል።

BACK



፬· ልጁ ፈቃዱን ለመስጠት የማይችል ወይላይ የሚቆጠር ወላጅ የሌለው እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ለልጁ ያለውን ጠቃሚነት ግምት ውስጥ በማስገባት የጉዲፈቻ ስምምነቱን ሊያፀድቀው ይችላል።

## አንቀጽ ፩፻፺፱ ስለመንግሥት ወይም የግል ዕጓለማውታን አሳዳጊ ተቋሞች

፩· የመንግሥት ወይም የግል ዕጓለማውታን አሳዳጊ ተቋሞች እያሳደጉት ያሉትን ማንኛውንም ልጅ ለጉዲፈቻ አድራጊዎች በስምምነት ለመስጠት ይችላሉ።

፪· ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ተቋሞች አንድን ልጅ በስምምነት ከመስጠታቸው በፊት የሕፃናትን ደህንነት ለመከታተል ሥልጣን ለተሰጠው የመንግሥት አካል ስለልጁ ማንነት ፡ ተቋሙ በምን ሁኔታ እንደተረከበውና ስለጉዲፈቻ አድራጊው ግላዊ ፡ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አቋም መግለጫ ማቅረብ አለባቸው።

## አንቀጽ ፩፻፺፲ ጉዲፈቻ አድራጊው የውጭ ዜጋ ሲሆን

፩· ጉዲፈቻ አድራጊው የውጭ ዜጋ ሲሆን ፡ የሕፃናትን ደህንነት ለመከታተል ሥልጣን የተሰጠው አካል ስለጉዲፈቻ አድራጊው ግላዊ ፡ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አቋም አግባብ ያላቸውን መረጃዎች በማጠናቀርና በመመርመር ስምምነቱ በይደረግ ለልጁ ጠቃሚነት ይኖረዋል ሲል አስተያየቱን ካልሰጠ በስተቀር የጉዲፈቻውን ስምምነት ፍርድ ቤት ሊያፀድቀው አይችልም።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ቢኖርም ፡ ፍርድ ቤቱ ስምምነቱ ለልጁ ጠቃሚነት አይኖረውም ሲል የገመተ እንደሆነ የባለሥልጣኑን አስተያየት ባለመቀበል ስም ምነቱን ላያፀድቀው ይችላል።

፫· ፍርድ ቤቱ ከባለሥልጣኑ የቀረበለት መረጃ በቂ መስሎ ያልታየው እንደሆነ ፡ አዲስ ምርመራ በማከናወን ተጨማሪ መረጃ እንዲቀርብለት ባለሥልጣኑን ለማዘዝ ፡ እንዲሁም ፡ ሌሎች ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች አስፈላጊ መስሎ የሚታያቸውን በእጃቸው የሚገኘውን መረጃ እንዲያቀርቡ ወይም እንደአስፈላጊነቱ የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ ለማዘዝ ይችላል።

## አንቀጽ ፩፻፺፬ የፍርድ ቤት ሥልጣን

፩· የጉዲፈቻ ስምምነት ፍርድ ቤት ካላፀደቀው በስተቀር ውጤት አይኖረውም።

፪· ፍርድ ቤቱ የጉዲፈቻ ስምምነቱን ከማጽደቁ አስቀድሞ በወሳኝ መልኩ ለልጁ መልካም አስተዳደግና ጥቅም የሚበጅ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

፫· በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፩፻፺፪ እና ፩፻፺፫ የተመለከቱትና የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤቱ የጉዲፈቻ ስምምነቱን ከማጽደቁ በፊት የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡

ሀ) ልጅየው ስለጉዲፈቻ ስምምነቱ ያለውን አስተያየት፡

ለ) አስቀድሞ ፈቃዱን ያልሰጠ ከሆነም የአሳዳሪውን አስተያየት፡

ሐ) ጉዲፈቻ አድራጊው ልጁን ለማሳደግና ለመንከባከብ ያለውን ብቃት፡

መ) ጉዲፈቻ አድራጊው የውጭ ዜጋ ሲሆን ልጅየው ኢትዮጵያ ውስጥ የሚያድግበት ሁኔታ አለመኖሩን፡

ሠ) ጉዲፈቻ አድራጊው እንደልጁ አድርጎ እንደሚያሳድገውና አላግባብ መጠቀሚያ እንደማያደርገው ለመገመት የሚያስችል መረጃ መኖሩን።

፬· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) በፊደል ተራ (ሠ) የተመለከተውን በሚያጣራበት ጊዜ፣ ጉዲፈቻ አድራጊው የውጭ ዜጋ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል።

### አንቀጽ ፩፻፺፫ የጉዲፈቻ ስምምነት የማይሰረዝ ስለመሆኑ

፩· የጉዲፈቻ ስምምነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ከተመለከተው ሁኔታ ውጪ ሊሰረዝ አይችልም።

፪· ጉዲፈቻ አድራጊው በጉዲፈቻ የተቀበለውን ልጅ እንደልጁ በማሳደግ ፋንታ በባርነት ወይም ባርነትን በሚመስል ሁኔታ ወይም ከግብረ ገብ ውጪ በሆኑ ተግባሮች እንዲሠማራ በማድረግ መጠቀሚያ ያደረገው እንደሆነ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የልጁን የወደፊት ሕይወት ክፉኛ በሚጎዳ አኳኋን የያዘው መሆኑን የተረዳ እንደሆነ ፡ ፍርድ ቤቱ የጉዲፈቻ ስምምነቱን ለመሠረዝ ይችላል።

### አንቀጽ ፩፻፺፬ የጉዲፈቻ ስምምነቱ እንዲሰረዝ አቤቱታ ስለማቅረብ

፩· የጉዲፈቻው ልጅ ራሱ፣ የሕጻናትን ደኅንነት ለመከታተል ሥልጣን የተሰጠው የመንግሥት አካል ወይም በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ማንኛውምሰው ከዚህ በላይ በተመለከተው አንቀጽ የተደነገገውን መሠረት በማድረግ የጉዲፈቻው ስምምነት እንዲሰረዝ አቤቱታ ለማቅረብ ይችላል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት አቤቱታ ሲቀርብለት፣ ፍርድ ቤቱ ጉዲፈቻ አድራጊውን ከማስቀረቡ በፊት ለአቤቱታው ምክንያት ናቸው የተባሉት መረጃዎች እውነት ሆነው ቢገኙ የጉዲፈቻ ስምምነቱን ለማፍረስ በቂ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት።

## ምዕራፍ አሥራ አንድ
## ቀለብ የመስጠት ግዴታ

### አንቀጽ ፻፺፯ ስለግዴታው ይዘት

በዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፺፰ ድንጋጌዎች መሠረት ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሰው እንደ ባለጉዳዮቹ ሁኔታና እንደ አካባቢው ልማድ የሚስማማውን በመከተል ለቀለብ ተቀባዩ ምግብ፡ መኖሪያ፡ ልብስ፡ ጤናውን የሚጠብቅበትና እንደሁኔታው ለትምህርት አስፈላጊ የሆነውን ነገር መስጠት አለበት።

### አንቀጽ ፻፺፰ ግዴታው በእነማን መካከል ስለመሆኑ

፩· በዚህ ሕግ አንቀጽ ፺፱ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡ ቀለብ የመስጠት ግዴታ የሚኖረው በቀጥታ ወላጆችና ተወላጆች ወይም በቀጥታ የጋብቻ ዘመዳሞች መካከል ነው።

፪· እንዲሁም በወንድማማቾች እና እህትማማቾች መካከልም ቀለብ የመስጠት ግዴታ ይኖራል።

### አንቀጽ ፻፺፱ ግዴታው ስለሚቀርበት ሁኔታ

ጋብቻው የፈረሰው በሞት ምክንያት ካልሆነ በስተቀር፡ በጋብቻ ዘመዳሞች መካከል ያለው ቀለብ የመስጠት ግዴታ ቀሪ ይሆናል።

### አንቀጽ ፪፻ ቀለብ ተቀባዩ መብቱን ስለሚያጣበት ሁኔታ

ቀለብ ተቀባዩ በቀለብ ሰጪው ወይም በዚህ ሰው ወደላይና ወደታች በሚቆጠሩ ወላጆች ወይም ተወላጆች ወይም ባል ወይም ሚስት ሕይወት ወይም ንብረት ላይ የወንጀል ተግባር የፈጸመ ወይም ለመፈጸም የሞከረ እንደሆነ ቀለብ የመቀበል መብቱን ያጣል ።

### አንቀጽ ፪፻፩ ግዴታው እንዲኖር አስፈላጊ ሁኔታዎች

ቀለብ የመስጠት ግዴታ ተፈጻሚ የሚሆነው ቀለብ ጠያቂው ሥርቶ ለኑሮው አስፈላጊ የሆነ ገቢ ለማግኘት አቅም የሌለውና በችግር ላይ የወደቀ ሲሆን ብቻ ነው።

## አንቀጽ ፪፻፪ ስለግዴታው አፈጻጸም

፩· በመሠረቱ ቀለብ የመስጠት ግዴታ የሚፈጸመው ቀለብ ሰፋጪው ለቀለብ ተቀባዩ የቀለቡን ገንዘብ በመስጠት ነው።

፪· የቀለቡ መጠን የሚወሰነው ቀለብ ጠያቂው ያለበትን ችግር እና የቀለብ ሰፋጪውን አቅም በማመዛዘን ነው።

## አንቀጽ ፪፻፫ ሁኔታውን ማሻሻል የሚቻል ስለመሆኑ

ቀለብ ሰፋጪው ወይም ተቀባዩ በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ስለቀለቡ መጠን ወይም ስለቀለብ ተቀባዩ መኖሪያ የተሰጠውን ውሳኔ በማናቸውም ጊዜ ማሻሻል ይቻላል።

## አንቀጽ ፪፻፬ ቀለቡ ስለሚከፈልበት ቦታ

ቀለቡ የሚከፈለው በተቻለ መጠን ለቀለብ ተቀባዩ በሚያመቸው ቦታ ይሆናል።

## አንቀጽ ፪፻፭ (፩) የቀለብ ገንዘብ ሊተላለፍና ሊያዝ የማይችል ስለመሆኑ

፩· ለቀለብ የሚከፈል ገንዘብ ሊተላለፍ ወይም ሊያዝ አይችልም።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም፣ ለቀለብ የሚከፈል ገንዘብ የሚከፈልበት ጊዜ ከመድረሱ አስቀድሞ ቢሆንም እንኳን ቀለብ ተቀባዩ ላለበት ችግር አሳቢ ለሚሆኑ ለዕርዳታ ለተቋቋሙ ድርጅቶች ሊተላለፍ ይችላል።

፫· እንዲሁም የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ለቀለብ ተቀባዩ ኑሮ አስፈላጊ የሆነውን ነገር ያበደሩ ሌሎች ሰዎችን በተመለከተ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

## አንቀጽ ፪፻፮ (፪) የቀለብ ገንዘብ የማይጠራቀም ስለመሆኑ

ቀለብ ተቀባዩ ለኑሮው አስፈላጊ መሆኑን ካላረጋገጠ በስተቀር፣ የቀለቡን ገንዘብ መቀበል ካለበት ቀን ጀምሮ በተከታዮቹ ሦስት ወራት ውስጥ ያልተቀበለው ወይም ሳይጠይቀው የቀረ እንደሆነ የተጠራቀመው ቀለብ እንዲሰጠው መጠየቅ አይችልም።

**አንቀጽ ፪፻፮ ቀለብ ተቀባዩን በቀለብ ሰጪው ቤት ለማኖር ስለመቻል**

፩· ቀለብ ሰጪው ቀለብ ተቀባዩን በመኖሪያ ቤቱ ተቀብሎ በማስቀመጥ ቀለብ የመስጠት ግዴታውን ሊፈጽም ይችላል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ስለተመለከተው ጉዳይ ክርክር የተነሳ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የነገሩን የአካባቢ ሁኔታዎች በመመልከት ተገቢ መስሎ የታየውን ይወስናል።

፫· ቀለብ ሰጪው ቀለብ ተቀባዩን በመኖሪያ ቤቱ እንዲያስቀምጥ ምንጊዜም ቢሆን አይገደድም።

**አንቀጽ ፪፻፯ ስለቀለብ ሰጪዎች ብዛት (፩) መሠረቱ**

ለቀለብ ተቀባዩ ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለባቸው ሰዎች ብዙ የሆኑ እንደሆነ ቀለብ ተቀባዩ ከእነርሱ መካከል አንዱ ቀለቡን እንዲሰጠው ሊጠይቀው ይችላል።

**አንቀጽ ፪፻፰ (፪) ስለአቤቱታ**

፩· ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለባቸው ሰዎች ብዙ ሆነው ከእነርሱ መካከል አንዱ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑት ቀለቡን የከፈሉ እንደሆነ፣ ሳይከፍሉ የቀሩት ድርሻቸውን እንዲከፍሏቸው ለመጠየቅ ይችላሉ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ስለተመለከተው ጉዳይ ክርክር የተነሳ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተካሳሾቹ ያላቸውን ሀብትና ከከሳሽ ጋር ያላቸውን የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ደረጃ በማመዛዘን ተከሳሾቹ የቀለቡን ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲከፍሉ ሊወስንባቸው ይችላል ።

**አንቀጽ ፪፻፱ (፫) ለቀለብ ሰጪዎች የሚሰጥ የከፋይነት ተራ**

በዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፺፯ መሠረት ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለባቸው ሰዎች ቅደም ተከተል፣

ሀ) በመጀመሪያ ደረጃ፣ ባል ወይም ሚስት፣

ለ) በሁለተኛ ደረጃ፣ ተወላጆች እንደየደረጃቸው፣

BACK



ሐ) በሦስተኛ ደረጃ፡ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች እንደየደረጃቸው፡

መ) በአራተኛ ደረጃ፡ ወንድማማችና እህትማማቾች፡

ሠ) በአምስተኛ ደረጃ፡ የጋብቻ ተወላጆች እንደየደረጃቸው፡

ረ) በስድስተኛ ደረጃ፡ የጋብቻ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች እንደየደረጃቸው።

አንቀጽ ፪፻፲፩ በጋራ ቀለብ ሰጪዎች መካከል የሚደረግ ስምምነት

፩· የጋራ ቀለብ ሰጪዎች እርስ በእርሳቸው ስለአላቸው ግንኙነት፡ ለጋራ ቀለብ ተቀባያቸው ከእነርሱ መካከል አንዱ ቀለቡን እንዲሰጠው በማለት የሚፀና ስምምነት ለማድረግ ይችላሉ።

፪· ቀለብ ተቀባዩ ስምምነቱን ወዶ የተቀበለ እንደሆነ፡ ይህንን ስምምነት የማያከብርበት ከባድ ምክንያት ካልተገኘ በስተቀር ቀለቡን ከሌሎቹ ቀለብ ሰጪዎች መጠየቅ አይችልም።

አንቀጽ ፪፻፲፪ ስለጉዲፈቻ ልጅ ልዩ ሁኔታ

፩· የጉዲፈቻ ልጅ ባል ወይም ሚስትና የቀጥታ መስመር ተወላጆች የጉዲፈቻ አድራጊው ቤተዘመዶች ቀለቡን መስጠት በማይችሉበት ሁኔታ ካልተገኙ በስተቀር፡ የሥጋ ወላጆቹን ቤተዘመዶች ቀለብ ለመጠየቅ አይችሉም።

፪· የቀደምት ቤተሰቦቹ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ቀለብ ለማግኘት ከዘመዶቻቸው አንዱን ለመጠየቅ የማይችሉ ካልሆነ በስተቀር በጉዲፈቻ የሰጡትን ልጅ ቀለብ ሊጠይቁት አይችሉም።

አንቀጽ ፪፻፲፫ ስለ ሥርዓተ ቀብር ወጪ

፩· ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሰው ለዚህ ለተባለው ሰው ሥርዓተ ቀብር የወጣውንም ወጪ ለመክፈል ይገደዳል።

፪· ይህን ወጪ ያደረገው ሰው፡ ወጪውን እንዲተካለት ቀለብ ሰጪውን ለመጠየቅ ይችላል።

## አንቀጽ ፪፻፲፬ ልዩ ስምምነቶች

ልዩ ስምምነቶችን በማድረግ በዚህ ምዕራፍ የተጻፉትን ድንጋጌዎች ለመለወጥ አይፈቀድም።

## ምዕራፍ አሥራ ሁለት
## አካለ መጠን ስላልደረሱ ሰዎች
## ክፍል ፩
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## አንቀጽ ፪፻፲፭ ትርጓሜ

አካለ መጠን ያልደረሰ ሰው ማለት ጾታ ሳይለይ ዕድሜው አሥራ ስምንት ዓመት ያልሞላው ልጅ ነው።

## አንቀጽ ፪፻፲፮ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ችሎታ የሌለው ስለመሆኑ

፩· አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ስለመልካም አስተዳደጉና ደህንነቱ ጉዳይ በአንድ አሳዳሪው እየተጠበቀ ይቆያል።

፪· ንብረት ነክ ጥቅሞቹንና በአጠቃላይ የንብረቱን አስተዳደር በሚመለከት በሞግዚቱ ይወከላል።

፫· በሕግ በግልጽ ለተመለከቱ ጉዳዮች ካልሆነ በስተቀር፣ አካለ መጠን ያልደረሰ ሰው ሕጋዊ ድርጊቶችን ለመፈፀም አይችልም።

## አንቀጽ ፪፻፲፯ የዕድሜ ማስረጃ

፩· የአንድ ሰው ዕድሜ የሚረጋገጠው በልደት ምስክር ወረቀት ነው።

፪· የልደት ምስክር ወረቀት የሌለ እንደሆነ ዕድሜውን በአስተማማኝነት ለማረጋገጥ ያስችላሉ በሚባሉ ሰነዶች ወይም ከሁለት ያላነሱ ምስክሮችን ቃል መሠረት በማድረግ ፍርድ ቤት ዕድሜውን ይወስናል።

## አንቀጽ ፪፻፲፰ ውሳኔ ሰጪ አካላት መከተል ስላለባቸው መርህ

በዚህ ምዕራፍ መሠረት በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ የሚሰጡ ውሳኔዎች ሁሉ ለልጆች ደህንነትና መልካም አስተዳደግ የሚበጁ መሆን ይኖርባቸዋል ።

## ክፍል ፪
## አካለመጠን ያልደረሰን ልጅ ስለሚጠብቁ ተቋሞች

## አንቀጽ ፪፻፲፱ የወላጆች ሥልጣን

አባትና እናት ጋብቻቸው ፀንቶ ባለበት ጊዜ ሁሉ አካለመጠን ላልደረሱት ልጆቻቸው የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት የጋራ ሥልጣን ይኖራቸዋል ።

## አንቀጽ ፪፻፳ ከወላጆች የአንዱ ብቁ አለመሆን

፩· ከወላጆቹ አንዱ የሞተ፣ ችሎታ ያጣ፣ የተገቢነት መብት ያጣ፣ ወይም ከቤተሰብ አስተዳዳሪነት መብቱ የታገደ እንደሆነ የአሳዳሪነትና ሞግዚትነት ሥልጣኑን ይዞ የሚቆየው አንደኛው ወገን ብቻ ይሆናል።

፪· እንዲሁም የልጁ አባት ያልታወቀ በሆነ ጊዜ የዚህን ሥልጣን ሥራ የምትፈፅመው እናቱ ብቻ ትሆናለች።

## አንቀጽ ፪፻፳፩ የልጁ አባትና እናት መፋታት

፩· በዚህ ሕግ አንቀጽ ፸፯ መሠረት ባልና ሚስት በስምምነት ሲፋቱ፣ የልጆቻቸውን አሳዳሪነትና ሞግዚትነት በተመለከተ በስምምነት ይወስናሉ ።

፪· በማናቸውም የፍቺ ሁኔታ የልጆቻቸውን አሳዳሪነትና ሞግዚትነት ባልና ሚስቱ በስምምነት ሊወስኑ ካልቻሉ ፣ ፍቺውን የወሰነው ፍርድ ቤት ስለልጆቹ አሳዳሪና ሞግዚትም አብሮ ይወስናል ።

BACK



## አንቀጽ ፪፻፳፪ በኑዛዜ ቃል የተመረጠ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት

### (፩) መሠረት፡

፩· አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ በህይወት ያለው ወላጅ ከጊዜ ሞት፡ በኋላ ልጁን የሚያስተዳድር ወይም ለልጁ ሞግዚት የሚሆነውን ሰው በመጨረሻ የኑዛዜ ቃል ለመምረጥ ይችላል።

፪· እንዲሁም የአሳዳሪውን ወይም የሞግዚቱን ሥልጣን ለመወሰንና የአሳዳጊነቱን የሥራ አመራር ሥልጣን በተወሰነ ሁኔታ ብቻ ለመስጠት ይችላል ።

## አንቀጽ ፪፻፳፫ (፪) አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ለመሾም የሚፈፀም ግዴታ

አባት ወይም እናት በህይወት ሳለ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ የአሳዳሪነት ወይም ሞግዚትነት ሥራ ያካሂድ የነበረ ካልሆነና በዚሁም ጊዜ በገዛ ፈቃዱ ሥልጣኑን አውቆ የተወ ካልሆነ በስተቀር በዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፳፪ ለአባት ወይም ለእናት የተሰጠው መብት አይኖረውም።

## አንቀጽ ፪፻፳፬ (፫) ለፍርድ ቤት አቤቱታ ስለማቅረብ

አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ጥቅም የሚያስገድድ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ፡ ስለ አሳዳሪው ወይም ስለሞግዚቱ አባቱ ወይም እናቱ ያደረጉትን ውሳኔ ፍርድ ቤት ሊሽረው ወይም ሊያሻሽለው ይችላል።

## አንቀጽ ፪፻፳፭ የልጅን አሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥልጣን ሊይዙ የሚገባቸው ዘመዶች (፩) ሊከተሉት የሚገባ ቅደም ተከተል

አንድ ልጅ አባትና እናት የሌለው እንደሆነና ከሁለቱ በመጨረሻ የሞተው ወላጅ በሚገባ ሁኔታ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ሳያደርግለት ቀርቶ እንደሆነ ለልጁ አሳዳሪነት ወይም ሞግዚትነት በሕጉ መሠረት

BACK



የሚመረጡና ይህ ሥልጣን የሚሰጣቸው ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ሰዎች ናቸው፡

ሀ) የልጁ ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች፡

ለ) እነዚህ በሌሉ ጊዜ አካለመጠን የደረሱ የልጁ ወንድሞች ወይም እህቶች፡

ሐ) እነዚህ በሌሉ ጊዜ የልጁ አጐት ወይም አክስት።

## አንቀጽ ፪፻፷፯ (፪) ይህ ቅደም ተከተል ስለሚለወጥበት ሁኔታ

፩· ከዚህ በላይ በተመለከተው መሠረት ሥልጣን በሚሰጠው ሰው ምትክ ለልጁ የሥጋ ዝምድና ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው ማንኛውም ሰው የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥልጣን ይሰጠኝ ሲል ጥያቄ ለማቅረብ ይችላል ።

፪· ይህም ጥያቄ መቅረብ የሚገባው ቅደም ተከተሉ ለሚመለከታቸው ዘመዶች ሲሆን ፡ ስምምነት ካልተገኘ ግን ጉዳዩ ለፍርድ ቤት ይቀርባል።

፫· ጥያቄው መቅረብ ያለበት አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ይህን ሥልጣን መያዙ ከታወቀበት ቀን ጀምሮ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ይሆናል ።

፬· ጥያቄውን ለመቀበል ወይም ላለመቀበል መሠረት የሚሆነው የልጁ ደህንነትና ጥቅም ሊሆን ይገባል።

## አንቀጽ ፪፻፷፰ በሕግ የሚመረጡ ዘመዶች መታጣት

፩· ከዚህ በላይ ባሉት አንቀጾች የተመለከተውን መሠረት በማድረግ ለልጁ አንድ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ለማግኘት ያልተቻለ እንደሆነ ይህ ሥራና ሥልጣን ፍርድ ቤት ለመረጠው ሰው ሊሰጥ ይችላል ።

፪· ፍርድ ቤቱ ይህን ጉዳይ ለመወሰን የልጁ ዘመድ በሆነ ወይም ባልሆነ ያገባኛል ባይ በሚቀርብ ጥያቄ ሊመሰረት ይችላል ።

፫· የህፃናትን ደህንነት ለመከታተል ሥልጣን የተሰጠው የመንግሥት አካልም ጉዳዩን ለፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል ።

## አንቀጽ ፪፻፴፫ የፍርድ ቤት ምርጫ (፩) አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመዶች

ፍርድ ቤት ለልጁ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት እንዲሆን የሚመርጠውና ይህን ሥልጣን የሚሰጠው የልጁ የቅርብ የሥጋ ዘመድ የሆነን ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለውንና በተቻለም መጠን ይህን ሥራ ለማከናወን ችሎታና ፈቃደኛነት ያለውን ሰው ነው ።

## አንቀጽ ፪፻፴፬ (፪) የበጎ አድራጎት ድርጅት

ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነቱን ሥልጣን ለዚህ ዓይነት ጉዳይ ለተቋቋመ የበጎ አድራጎት ድርጅት ሊሰጥ ይችላል ።

## አንቀጽ ፪፻፴፭ ተመሳሳይ ሁኔታዎች

ከዚህ በላይ ለተገለጹት ድንጋጌዎች አፈፃፀም አንድ ሰው በሕግ ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ተግባሮቹን ለማከናወን የማይችል እንደሆነ እንደሌለ ይቆጠራል ።

## አንቀጽ ፪፻፴፮ የአሳዳሪው ወይም የሞግዚቱ መታወቂያ

፩· በመሠረቱ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ አሳዳሪ እንዲሆን ሥልጣን ተሰጥቶት የልጁን አሳዳሪነት የተቀበለው ሰው ሞግዚቱም ነው ።

BACK



፪· የነገሩ ሁኔታ ተቃራኒ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር በህይወት ያለው አባት ወይም እናት ወይም ፍርድ ቤት ለልጁ የሚሾሙት ሞግዚት ወይም አሳዳሪ፡ ሁለቱንም ሥልጣን እንደያዘ ይቆጠራል ።

## አንቀጽ ፪፻፴፪ ለአባትና ለእናት የተሰጠ መብት

አባት ወይም እናት ጉዳዩ ጠቃሚ መስሎ የታያቸው እንደሆነ የልጃቸውን የአሳዳሪነት ሥልጣን ራሳቸው ይዘው ሞግዚት ለመሾም ይችላሉ ።

## አንቀጽ ፪፻፴፫ ለፍርድ ቤት የተሰጠ ሥልጣን

ፍርድ ቤት የልጁን አሳዳሪና ሞግዚት የመሾም ሥልጣን በያዘበት ጊዜና ይህን \ ለማድረግ አሳማኝ ምክንያት ሲኖር፣ ከአሳዳሪው በተጨማሪ ሌላ ሞግዚት ለመሾም ይችላል ።

## አንቀጽ ፪፻፴፬ ምትክ ሞግዚት (፩) በሞግዚቱና አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ መካከል ስለሚነሳ የጥቅም ግጭት

፩· በሞግዚቱና አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ መካከል የጥቅም ግጭት የተነሳ እንደሆነ ፍርድ ቤት አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ ምትክ ሞግዚት ይሾምለታል ።

፪· ምትክ ሞግዚት የሚመረጠው በሞግዚቱ ወይም ወደላይ ከሚቆጠሩ የልጁ ወላጆች ወይም አካለመጠን ከደረሱ ወንድሞቹና እህቶቹ በአንዳቸው ጥያቄ አቅራቢነት ነው ።

**አንቀጽ ፪፻፴፫ (፪) አካለመጠን ባልደረሱ በብዙ ልጆች መካከል ስለሚነሳ የጥቅም ግጭት**

፩· አካለመጠን ባልደረሱ በብዙ ልጆች መካከል የጥቅም ግጭት የተፈጠረ እንደሆነና የነዚህም ተጠሪ ወኪል አንድ የጋራ ሞግዚት ብቻ በሆነ ጊዜ ከዚህ በላይ የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል ። (አንቀጽ ፪፻፴፩)

፪· የጥቅም ግጭቱ የሚፈታውም በሞግዚቱና በምትክ ሞግዚቱ መካከል በሚደረግ ስምምነት መሠረት ይሆናል ።

**አንቀጽ ፪፻፴፬ የሥራው አጀማመር**

፩· የአሳዳሪነቱ ወይም የሞግዚትነቱ ሥራ የሚጀመረው አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ በሕጉ መሠረት ወይም በፍርድ ውሳኔ ተመርጠው እንደተሾሙ ወዲያውኑ ነው ።

፪· ሆኖም የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራ የተሰጠው መሆኑን ከማወቁ በፊት አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ይህን ሥራውን ሳይጀምር ለደረሰው ጉዳት ሁሉ በኃላፊነት ሊጠየቅ አይችልም ።

**አንቀጽ ፪፻፴፭ ሥራው የግዴታ ስለመሆኑ**

የአሳዳሪነትን ወይም የሞግዚትነትን ሥራዎች እንዲያከናውን ተመርጦ የተሾመው ሰው ሥራውን የማከናወን ግዴታ አለበት ።

**አንቀጽ ፪፻፴፮ ሥራው እንዲቀርለት የሚቀርብ ጥያቄ**

፩· አንድ ሰው የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ተግባርን ማከናወን በራሱ ላይ ከበድ ያሉ ችግሮችን በአጠቃላይ

BACK



ኑሮውም ላይ እንቅፋት የሚያስከትልበት ከሆነ ሥራው እንዲቀርለት ፍርድ ቤትን ሊጠይቅ ይችላል ።

፪· እንዲሁም በተመሳሳይ ሁኔታ አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ከተሰጠው የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራው እንዲሻር ጥያቄ ማቅረብ ይችላል ።

## አንቀጽ ፪፻፴፱ በሕግ አግባብ የሚሰጥ ልዩ አስተያየት

በዚህ ሕግ መሠረት ለአሳዳሪነት ወይም ለሞግዚትነት ስለሚመረጡ ሰዎች የተደነገገው ቢኖርም፡ ከዚህ የሚከተሉት ሰዎች በአሳዳሪነት ወይም በሞግዚትነት እንዳይሾሙ ወይም እንዲሻሩ ጥያቄ ካቀረቡና ይህም ጥያቄ የራሳቸውን ልጆች የሚመለከት ካልሆነ በስተቀር የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራ እንዲሰሩ አይገደዱም፡

ሀ) ዕድሜው ስድሳ አምስት ዓመት የሞላው ሰው ፣

ለ) በውትድርና የተሰማሩ ሰዎች።

## አንቀጽ ፪፻፵ ለጊዜው ሥራውን የማከናወን ግዴታ

፩· የልጁ አሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራ ችግር ያደርስብኛል ብሎ ምክንያት በማቅረብ ይህ ኃላፊነት እንዲወገድለት የሚጠይቅ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት በዚህ ሥራ ሌላ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ተተክቶ ሥልጣኑን እስኪረከበው ድረስ የተሰጠውን ሥራ ለጊዜው የማከናወን ግዴታ አለበት ።

፪· እንዲሁም በሹመቱ ላይ ተቃውሞ የተነሳበት አሳዳሪ ወይም ሞግዚትም ተመሳሳይ ግዴታ ይኖርበታል ።

## አንቀጽ ፪፻፵፩ ስለ ሥራው መቅረት

፩· የአሳዳሪው ወይም የሞግዚቱ ሥራ ቀሪ የሚሆነው የሚጠበቀው ልጅ የሞተ እንደሆነ ወይም አካለመጠን በደረሰ ጊዜ ወይም ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ በወጣ ጊዜ ነው ።

፪· እንዲሁም አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ሲሞት ወይም ችሎታ ሲያጣ ወይም ብቁ ያለመሆኑ ሲገለጽ ወይም ከሥራው ሲሻር ቀሪ ይሆናል።

፫· አዲስ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ ሲሾምለትም የቀድሞዎቹ ተሿሚዎች ኃላፊነት ያበቃል።

## አንቀጽ ፪፻፵፪ ችሎታ ማጣት (፩) አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ

የራሱን ልጆች በሚመለከት ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ፣ አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራን ለማካሄድ ችሎታ የለውም ።

## አንቀጽ ፪፻፵፫ (፪) በፍርድ የተከለከሉ ሰዎች

፩· በፍርድ የተከለከለ ማንኛውም ሰው የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራን ለማከናወን አይችልም ።

፪· ይህን ሥራ ያከናውን የነበረ አንድ ሰው ችሎታ ያጣ መሆኑ በፍርድ ቤት ውሳኔ የተገለጸ እንደሆነ፣ የዚህ ሰው ሞግዚት በሕግ መሠረት የተከለከለውን ሰው ሥራ ተረክቦ በምትክነት ማካሄድ ለሚገባው ሰው ወዲያውኑ ማስታወቅ አለበት።

፫· እንዲህ ያለ ሰው የሌለም እንደሆነ በፍርድ የተከለከለው ሰው ምትክ እንዲደረግለት ሞግዚቱ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅረብ አለበት ።

BACK



## አንቀጽ ፪፻፵፬ ብቁ ስላለመሆን

፩· አንድ ሰው የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራን ለማካሄድ ብቁ አይደለም ብሎ ፍርድ ቤት ለመወሰን የሚችለው የወንጀል ተግባር በመፈጸሙ የግል ነፃነትን የሚከለክል የእስራት ወይም የሞት ቅጣት የተፈረደበት ሲሆን ነው።

፪· ፍርድ ቤት የዚህን ዓይነት ቅጣት በአንድ ሰው ላይ በሚወስንበት ጊዜ ነገሩ ተገቢ መሆኑን የገመተ እንደሆነ የተፈረደበት ሰው ለዚህ ሥራ ብቁ አለመሆኑን ጭምር ለመወሰን ይችላል።

## አንቀጽ ፪፻፵፭ (፩) የአሳዳሪው መሻር

፩· አካለመጠን ላልደረሰ ልጅ አሳዳሪ እንዲሆን የተሾመ ሰው ልጁ ለኑሮው አስፈላጊ የሆነውን ጥበቃ ሳያገኝ ወይም ከሞራል ጋር የሚስማማ የአእምሮ አስተዳደግ ወይም ከችሎታው ጋር ተመዛዛኝ የሆነ ትምህርት እንዲያገኝ ሳያደርግ ግለት የቀረ እንደሆነ አሳዳሪው እንዲሻር ፍርድ ቤት ሊወስን ይችላል።

፪· ይህንንም ውሳኔ ለመስጠት አሳዳሪው የሚኖርበትን የአካባቢ ሁኔታና ጊዜውንም መመርመርና መሠረት ማድረግ አስፈላጊ ነው።

፫· በተለይም ፍርድ ቤቱ አሳዳሪውን ለመሻር የሚችለው አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ወንጀል መስራቱ የተረጋገጠ ሲሆንና ይህንንም ወንጀል የፈፀመው በመጥፎ አስተዳደግ ወይም በአሳዳሪው ጉድለት ተገቢውን የግብረ ገብ ትምህርት ለማግኘት ባለመቻሉ የሆነ እንደሆነ ነው።

## አንቀጽ ፪፻፵፮ (፪) የሞግዚቱ መሻር

አካለመጠን ላልደረሰ ልጅ ሞግዚት የሆነ ሰው እንዲሻር ፍርድ ቤት የሚወስነው ሞግዚቱ የልጁን ንብረትና ሀብት በመጥፎ ሁኔታ

BACK



ያስተዳደረና አጠባበቁም በቂ ያልሆነ እንደሆነ፣ ወይም ልጁን በሞግዚትነት እንዲያስተዳድር ሥልጣን የሰጠው ሰው ወይም አካል የሰጠውን መመሪያና የንብረት አስተዳደር ሥርዓት ሳይጠብቅና ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ ወይም ዕዳ ለመክፈል ያለመቻሉ በፍርድ ውሳኔ የተረጋገጠ እንደሆነ ነው።

## አንቀጽ ፪፻፺፯ (፫) የወላጆች መሻር

፩· የልጁ አባት ወይም እናት ወይም ሌሎች ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆቹ ከልጃቸው አሳዳሪነት ወይም ሞግዚትነት ስራቸው እንዲሻሩ መወሰን ሲያስፈልግ ፍርድ ቤቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅበታል።

፪· ፍርድ ቤቱ በዚህ ጉዳይ ላይ የሰጠውን ውሳኔ በተሻረው ወገን ጠያቂነት በማንኛውም ጊዜ እንደገና ሊመረምረው ይችላል።

## አንቀጽ ፪፻፺፰ (፬) ሥነ ሥርዓት

፩· አንድ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት እንዲሻር የሚቀርበው ጥያቄ በማናቸውም በጉዳዩ ያገባኛል ባይ ወገን ወይም በዐቃቤ ሕግ በኩል ሊቀርብ ይችላል።

፪· ፍርድ ቤቱ አሳዳሪውን ወይም ሞግዚቱን ለመሻር ከመወሰኑ በፊት በርሱ በኩል ያለውን ሀሳብ ሊያዳምጠው ይገባል።

፫· ሆኖም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተውን ሲያከናውን በልጁ ደህንነት ወይም ሀብት ላይ ተጨማሪ ጉዳት ይደርሳል ተብሎ የሚገመት ከሆነ ፍርድ ቤቱ ተገቢ መስሎ የታየውን ጊዜያዊ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

## አንቀጽ ፪፻፺፱ የፍርድ ቤት ኃላፊነት

፩· ፍርድ ቤት አንድን ሰው አካለመጠን ላልደረሰ ልጅ አሳዳሪነት ወይም ሞግዚትነት ለመሾም ሲመርጥ ወይም የተሾመውን

BACK



ከሥራው ሲሸር ከውሳኔው በፊት በተቻለ መጠን ከልጁ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ፡ አካለመጠን ከደረሱ ወንድ ሞቹና እህቶቹ ጋር መመካከር ይገባዋል ።

፪· አስፈላጊ መስሎ ሲታየው አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ያለውን ሀሳብ ሊያዳምጥ ይችላል።

፫· ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን ሲሰጥ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ጥቅም የማይጎዳልበትን አሠራር ብቻ መከተል እንጂ የቀረቡለትን ሀሳቦች የመቀበል ግዴታ አይኖርበትም።

## አንቀጽ ፪፻፶ ሥራው ያለ ክፍያ የሚከናወን ስለመሆኑ

፩· የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት ሥራ የሚከናወነው ማናቸውም ዋጋ ሳይከፈልበት በነፃ ነው።

፪· ሆኖም አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ሥራውን ለማከናወን ረጅም ጊዜ የሚጠይቀው የሆነ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ አንድ የተወሰነ አበል ሊቆረጥለት ይችላል።

፫· ይህም አበል አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ የሀብት ገቢ ላይ ካልሆነ በስተቀር ከሌላ ሀብት ሊወሰድ አይችልም፡ የአበሉም ልክ ከጠቅላላው የሀብት ገቢ ሲሶ ሊበልጥ አይችልም።

## አንቀጽ ፪፻፶፩ የሥራው አካሄድ የግል ስለመሆኑ

፩· የአሳዳሪነቱ ወይም የሞግዚትነቱ ሥራ የግል ጠባይ የያዘ ስለሆነ ሥራውን የሚያከናውነው ራሱ እንጂ ለአሳዳሪው ወይም ለሞግዚቱ ወራሾች ሊተላለፍ አይችልም።

፪· ወራሾቹ በኃላፊነት የሚጠየቁት አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ በፈፀመው የሥራ አካሄድ ጉድለት ብቻ ነው። ይኸውም በውርስ ሕግ መሠረት ይወሰናል።

## አንቀጽ ፪፻፶፪ የወራሾች ግዴታ

፩· የአንድ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ወራሾች ፡ አሳዳሪው ወይም

ሞግዚቱ እንደሞተ ወዲያውኑ በዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፸፫ በተመለከተው መሠረት ለሟቹ ምትክ ሊሆን ለሚገባው ሰው የማስታወቅ ግዴታ አለባቸው።

፪· የዚህ ዓይነት ሰው የሌለ እንደሆነ ፡ በሟቹ ምትክ የሚመረጠው ሰው እንዲሾም ለፍርድ ቤት ማስታወቅ አለባቸው።

፫· የአሳዳሪው ወይም የሞግዚቱ ወራሾች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተመለከቱትን ግዴታዎች እስኪወጡ ድረስ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅም ሆነ ለሌላ ሦስተኛ ወገኖች ኃላፊዎች ሆነው ይቆያሉ ።

## አንቀጽ ፪፻፹፫ የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት ማስረጃ

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አሳዳሪነቱን ወይም ሞግዚትነቱን የሚያስረዳት ጽሑፍ እንዲሰጠው ፡ አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ፍርድ ቤትን ለመጠየቅ ይችላል።

## አንቀጽ ፪፻፹፬ ከሞግዚት ጋር የሚመሳሰል ሁኔታ

ሞግዚትን የሚመለከቱት የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች በምትክ ሞግዚት ጉዳይም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

## ክፍል ፫

## የአሳዳሪውና የሞግዚቱ ሥልጣን

### ንዑስ ክፍል ፩

### አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ አስተዳደግና ጥበቃ

## አንቀጽ ፪፻፹፭ አሳዳሪው የመንግሥት ተቋማትን እገዛ መጠየቅ ስለመቻሉ

አሳዳሪው ከዚህ በታች በተመለከቱት አንቀጾች የተሰጠውን ሥልጣን በሥራ ላይ ለማዋል እንዲችል አግባብነት ያላቸውን የመንግሥት ተቋሞች እገዛ ሊጠይቅ ይችላል።

BACK



## አንቀጽ ፪፻፶፮ አካለመጠን ስላልደረሰ ልጅ መኖሪያ ቦታ

፩· አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ መኖሪያ ቦታ ይወስናል።

፪· አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ያለአሳዳሪው ፈቃድ የተመደበለትን መኖሪያ ቦታ ሊተው አይችልም።

፫· አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ የተመደበለትን መኖሪያ ቦታ ትቶ የሄደ እንደሆነ፡ አሳዳሪው ወደ መኖሪያ ቦታው እንዲመለስ ሊያስገድደው ይችላል።

## አንቀጽ ፪፻፶፯ አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ጤና አጠባበቅ

፩· አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ጤንነት ሁኔታ ይከታተላል።

፪· አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ሲታመም ከህመሙ እንዲፈወስ አስፈላጊውን እርምጃ ሁሉ ይወስዳል።

## አንቀጽ ፪፻፶፰ አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ አስተዳደግ

፩· አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ አስተዳደግ ይመራል።

፪· አሳዳሪው አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ መልካም አስተዳደግ ተገቢነት ያለውን የዲሲፕሊን እርምጃ ለመውሰድ ይችላል።

## አንቀጽ ፪፻፶፱ አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ማህበራዊ ግንኙነት

፩· አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ማህበራዊ ግንኙነት ይመራል ፡ ይቆጣጠራል ።

፪· ሆኖም ፡ አሳዳሪው በቂ ምክንያት ሳይኖረው አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ወደላይ ከሚቆጠሩ ወላጆቹ ጋር ግንኙነት እንዳያደርግ ሊያግደው አይችልም።

## አንቀጽ ፪፻፺ አጠቃላይ እና የሙያ ትምህርት የመስጠት ግዴታ

አሳዳሪው አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ ዕድሜና ችሎታ ተመጣጣኝ የሆነ አጠቃላይ ትምህርት ወይም የሙያ ሥልጠና እንዲያገኝ ማድረግ አለበት።

## አንቀጽ ፪፻፺፩ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ገቢ (፩) መሠረቱ

፩· አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ገቢዎች በመቀበል ለልጅየው ጥቅም ያውላል።

፪· አሳዳሪው ገንዘቡን ለምን አገልግሎት እንዳዋለው መግለጫ ለመስጠት አይገደድም።

## አንቀጽ ፪፻፺፪ (፪) ከፍተኛ ስለሆነ ገቢ

፩· አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ገቢ ከፍተኛ ሲሆንና አሳዳሪው የልጁ አባት ወይም እናት ያልሆነ እንደሆነ ፡ ፍርድ ቤት በዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፺፩(፪) የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚ እንዳይሆን ሊያግድ ይችላል።

፪· ፍርድ ቤቱ ትእዛዙን በሚሰጥበት ጊዜ፡ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ አስተዳደግና ለትምህርቱ በቂ ነው የሚለውን የገንዘብ መጠንና የሚከፈልበትን ጊዜ በመወሰን ለአሳዳሪው እንዲሰጠው ያደርጋል።

፫· ተራፊውን ገንዘብ በአትራፊ ሥራ ላይ እንዲያውለው በሞግዚቱ እጅ ተቀማጭ ይደረጋል።

## አንቀጽ ፪፻፺፫ (፫) አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ከሥራው ስለሚያገኘው ገቢ

፩· አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ዕድሜው ከ፲፭ ዓመት በላይ ሲሆን ከሥራው የሚያገኘውን ገቢ እራሱ ይቀበላል።

፪· ለራሱ ቀለብ የሚሆነውን ለአሳዳሪው ከሰጠ በኋላ፡ ቀሪውን ገንዘብ በዚህ ሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ሊጠቀምበት ሙሉ ነፃነት አለው።

## አንቀጽ ፪፻፹፬ (፬) በስጦታ ወይም በውርስ ስለተላለፉ ሀብቶች

፩· አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ በስጦታ ወይም በውርስ ሀብት የሚያስተላልፍ፡ ሰው ልጁ አካለመጠን ሳይደርስ አሳዳሪው ተቀብሎ ጥቅም ላይ እንዳያውለው ሊያግዝ ይችላል።

፪· በስጦታው ውል ወይም በኑዛዜው፣ ስለንብረቱ አስተዳደርና ስለሚገኘውም ገቢ የተመለከቱ ኃይለ ቃሎች ተፈፃሚ መሆን አለባቸው።

## አንቀጽ ፪፻፹፭ የመክፈያ ጊዜያቸው ያልደረሱ ገቢዎች

የመክፈያ ጊዜያቸው ያልደረሱ ገቢዎችን አሳዳሪው ግዴታ ሊገባ ባቸው አይችልም።

## አንቀጽ ፪፻፹፮ ስለወላጆች ሥልጣን

፩· አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ አባትና እናት በጋራ አሳዳሪዎቹ በሆኑ ጊዜ የአሳዳሪነት ተግባራቸውን በመመካከርና በመግባባት ይወጣሉ።

፪· አባት እና እናት ያለመግባባታቸውን በግላቸው ወይም በሽምግልና ለመፍታት ያልቻሉ እንደሆነ፡ ከሁለቱ አንደኛው በሚያቀርበው አቤቱታ መነሻነት ፍርድ ቤቱ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ ጥቅም ቅድሚያ በመስጠት ውሳኔ ይሰጣል።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ፡ አባትና እናት በአሳዳሪነታቸው በሚሰጡት ውሳኔ ላይ አቤቱታ ሊቀርብበት አይችልም።

BACK



## አንቀጽ ፪፻፺፯ የወላጆች መለያየት

ወላጆች በመለያየታቸው ምክንያት የአሳዳሪነት ስልጣን የአን ደኛው ወላጅ ብቻ የሆነ እንደሆነ ፡ ይኸው ወላጅ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የአሳዳሪነት ተግባር በማከናወን ላይ የሌለው ወገን፡ ወደላይ ከሚቆጠሩ ወላጆቹ ወይም አካለመጠን ከደረሱ ወንድሞቹና እህቶቹ አንዳቸው አቤቱታ ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላሉ።

## አንቀጽ ፪፻፺፰ አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ወላጅ በማይሆንበት ጊዜ

አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ወላጅ ያልሆነ እንደሆነ ፡ በልጁ አስተዳደግ ረገድ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ከወላጆቹ አንዳቸው ወይም ሌላ በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ሰው ወይም ዐቃቤ ሕግ ለፍርድ ቤት አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል ።

## ንዑስ ክፍል ፪
## አካለመጠን ያልደረሰን ልጅ ንብረት ስለማስተዳደር

## አንቀጽ ፪፻፺፱ መሠረቱ

፩· ሀብቱንና ንብረት ነክ ጥቅሞቹን በተመለከተ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ በሞግዚቱ ይወከላል ።

፪· ሀብቱንና ንብረት ነክ ጥቅሞቹን በማስከበርና በማስተዳደር ረገድ ሞግዚቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ የማድረግ ግዴታ አለበት ።

## አንቀጽ ፪፻፸ የንብረት ቆጠራና የዋጋ ግምት (፩) ሞግዚቱ የሞግዚትነት ሥራውን ከጀመረ በኋላ

፩· ሞግዚቱ፡፡ የሞግዚትነቱን ሥራ ከጀመረ በኋላ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ፡ ሦስት ምስክሮች ባሉበት አካለመጠን ያልደረ ሰውን ልጅ ንብረት ይቆጥራል ፡ የዋጋውንም ግምት ያወጣል።

፪· ሞግዚቱ አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ የሚጠይቀው ዕዳ ሲኖር ፡ በንብረት ቆጠራው መዝገብ በወቅቱ ካላሰፈረው በስተቀር የዕዳው ክፍያ ቀሪ ይሆንበታል ።

## አንቀጽ ፪፻፹፩ (፪) አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ የውርስ ሀብት

፩· አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ወራሽ በሚሆንበት ጊዜ ፡ ሞግዚቱ ስለልጁ ሆኖ ውርሱን ከመቀበሉ አስቀድሞ ሶስት ምስክሮች ባሉበት የውርስ ንብረቱን ቆጠራ ያከናውናል ፡ የዋጋውንም ግምት ያወጣል ።

፪· ሞግዚቱ ከውርሱ ሀብት ውስጥ ድርሻ ያለው እንደሆነ ፡ ይህንኑ በንብረት ቆጠራው መዝገብ ያላሰፈረው እንደሆነ ድርሻው ቀሪ ይሆንበታል ።

፫· የንብረት ቆጠራው ባለመከናወኑ ወይም በአግባቡ ባለመሠራቱ ለሚደርስ ጉዳት ሞግዚቱ በኃላፊነት ይጠየቅበታል ።

## አንቀጽ ፪፻፹፪ የሞግዚቱ ንብረት አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ ንብረት ጋር ስለሚቀላቀልበት ሁኔታ

፩· ሞግዚቱ፡ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረት ከግል ንብረቱ ጋር እንዳይቀላቀል አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሁሉ ማድረግ አለበት ።

፪· በተለይም ፡ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ገንዘብ ሞግዚቱ በራሱ የባንክ ሂሳብ ማስቀመጥ ወይም እንዲቀመጥ ማድረግ አይፈቀድለትም ።

## አንቀጽ ፪፻፹፫ የገንዘብ ሰነዶችና ሌሎች ውድ ዕቃዎች ስለሚቀመጡበት ሁኔታ

አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት በማስተዳደር ረገድ ችግር የሚፈጥር ካልሆነ በስተቀር፣ የገንዘብ ሰነዶችን፣ ውድ ዕቃዎችን፣

ጠቃሚ ጽሑፎችንና ሌሎች ተመሳሳይ ነገሮችን ሁሉ ሞግዚቱ ሊጠፉ ወይም ሊባክኑ በማይችሉበት አስተማማኝ ሥፍራ ማስቀመጥ አለበት።

## አንቀጽ ፪፻፸፬ የፍርድ ቤት ሥልጣን

፩· አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ሞግዚት የልጁ ወላጅ ባልሆነ ጊዜ ፡ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ሀብት መልካም አስተዳደር በሚመለከት ለሞግዚቱ መመሪያ እንዲሰጥ የልጁ ወደላይ ከሚቆጠሩ ወላጆች ወይም አካለመጠን ከደረሱ ወንድሞቹ ወይም እህቶቹ አንዳቸው ለፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ ።

፪· ፍርድ ቤቱም አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ሀብት አጠቃላይ ሁኔታ ፡ የሞግዚቱን ችሎታና የልጅየውን ጥቅም በማመዛዘን ስለሀብቱ አስተዳደር ጠቃሚ መስሎ የሚታየውን መመሪያ ይሰጠዋል ።

## አንቀጽ ፪፻፸፭ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ በስጦታ ወይም በውርስ ስለሚተላለፍ ንብረት

፩· አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ በስጦታ ወይም በውርስ ንብረት የሚያስተላልፍ ሰው፣ የንብረቱን አስተዳደር በሚመለከት ተገቢ ናቸው የሚላቸውን የአሠራር መመሪያዎች ሞግዚቱ እንዲከተል ሊያዝ ይችላል።

፪· የአሠራር መመሪያዎቹን ተከትሎ ለመስራት የማይቻል ወይም አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ጥቅም ላይ ጉዳት የሚያደርስበት መስሎ የታየው እንደሆነ ፣ ሞግዚቱ መመሪያዎቹ እንዲስተካከሉለት ፍርድ ቤትን ሊጠይቀ ይችላል።

## አንቀጽ ፪፻፹፯ ስለንግድ ድርጅቶችና ሌሎች መሰል ድርጅቶች

፩· የንግድ ፡ የኢንዱስትሪ ወይም ሌሎች መሰል ድርጅቶች አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ሀብት አካል የሆኑ እንደሆነ ፡ ወደላይ ከሚቆጠሩ ወላጆቹ ወይም አካለመጠን ከደረሱ ወንድሞቹና እህቶቹ አንዳቸው በሚያቀርቡት ጥያቄ፣ የልጁ አባት ወይም እናት ያልሆነው ሞግዚት ንብረቱን እንዲያጣራ ወይም እንዳለ እንዲቀጥል እንዲያደርግ ፍርድ ቤት ሊያዘው ይችላል ።

፪· ፍርድ ቤቱ ይህንን ትእዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ ሞግዚትነቱ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ ፡ የሞግዚቱን ችሎታና አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ጥቅም ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት ።

## አንቀጽ ፪፻፹፰ አንዳንድ ንብረቶችን ስለመሸጥ

፩· ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረት የሆኑ የሚንቀሳቀሱ ግዙፍ ንብረቶችን ፡ አክስዮኖችንና የገንዘብ ሰነዶችን ለመሸጥ ይችላል ።

፪· በልጁ አባት ወይም እናት ላይ ካልሆነ በስተቀር ፡ በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ማንኛውም ሰው ጥያቄ ሲያቀርብለት ፍርድ ቤት ስለሽያጩ መመሪያ ለመስጠት ወይም ሽያጩ እንዳይከናድ ለመከልከል ይችላል ።

## አንቀጽ ፪፻፹፱ ለአምጪው እንዲከፈል ስለሚሉ ሰነዶች

፩· አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ አባት ወይም እናት ያልሆነ ሞግዚት ለአምጪው እንዲከፈል የሚሉ ሰነዶች የልጁ ሀብት ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ በሶስት ወራት ውስጥ እንዲሸጡ ወይም

በልጁ ስም በተመዘገቡ ሰነዶች እንዲለወጡ ማድረግ አለበት።

፪· ሞግዚቱ ጥያቄ ሲያቀርብለት፣ ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከተው ግዴታ ነፃ እንዲሆን ሊያዝ ይችላል ።

## አንቀጽ ፪፻፸፱ ዕዳዎችና ገቢ ገንዘቦች

፩· ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ዕዳዎች ከልጁ ሀብት በመቀነስ ይከፍላል ።

፪· አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ መከፈል የሚገባውን ካፒታል እና ሌላ ገቢ ይቀበልለታል ፡ ስለመቀበሉ በማረጋገጥም ደረሰኝ ይሰጣል ።

## አንቀጽ ፪፻፹ ካፒታልን አትራፊ በሆነ ሥራ ላይ ስለማዋል (፩) የሞግዚቱ ግዴታ

፩· የገንዘቡ መጠን ከ፳፻ ብር በላይ የሆነ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ካፒታል ሞግዚቱ አትራፊ በሆነ ሥራ ላይ ማዋል አለበት ።

፪· ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን የገንዘብ መጠን ሊያሻሽለው ይችላል ።

## አንቀጽ ፪፻፹፩ (፪) የጊዜ ገደብ

፩· ካፒታሉ በሞግዚቱ እጅ በገባ በሶስት ወራት ውስጥ በአትራፊ ሥራ ላይ መዋል አለበት ።

፪· ፍርድ ቤቱ የጊዜውን መጠን ሊያሻሽለው ይችላል ።

BACK



## አንቀጽ ፪፻፹፪ ኃላፊነት

፩· በአትራፊ ሥራ ላይ ላላዋለው ገንዘብ ሞግዚቱ ሕጋዊ ወለዱን አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ መክፈል አለበት ።

፪· አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ተጨማሪ የጉዳት ካሣ እንዲከፍል ሊፈረድበት ይችላል ።

## አንቀጽ ፪፻፹፫ ገቢዎች

፩· አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ገቢዎች ፣ ገቢዎቹ በቂ ሆነው የማይገኙ ሲሆንም ከሀብቱ ቀንሶ ለአስተዳደጉና ለትምህርቱ አገልግሎት እንዲውል ሞግዚቱ ለአሳዳሪው ይሰጠዋል ።

፪· ፍርድ ቤቱ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በስተቀር ፣ ለዚህ አገልግሎት የሚውለው ገንዘብ በየወሩ ለአሳዳሪው ይከፈላል።

፫· የአከፋፈሉ ሁኔታ በአሳዳሪውና በሞግዚቱ ስምምነት ወይም በፍርድ ቤት በሚሰጥ ውሳኔ መሠረት ሊሻሻል ይችላል ።

## አንቀጽ ፪፻፹፬ የኪራይ ውሎች

በፍርድ ቤት ፈቃድ የተደረጉ ካልሆኑ በስተቀር ፣ ሞግዚቱ የሚያደርጋቸውን የኪራይ ውሎች ልጅየው አካለመጠን ከደረሰ ከሶስት ዓመታት በኋላ እንዲፈጽማቸው አይገደድም ።

## አንቀጽ ፪፻፹፭ ስለውርስ

፩· ልጁ በውርስ የሚያገኘውን ንብረት ሞግዚቱ ይቀበላል ።

፪· ሞግዚቱ የውርሱ ሀብት ዕዳውን ለመክፈል ፈጽሞ የማይችል ካልሆነ በስተቀር ውርሱን አልፈልግም ለማለት አይችልም ።

## አንቀጽ ፪፻፹፮ ስለስጦታ

፩· አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ የሚሰጠው ስጦታ ጠቃሚነት የለውም በማለት ካልሆነ በስተቀር ሞግዚቱ አልቀበልም ለማለት አይችልም ።

፪· በተለምዶ ከሚሰጡ አነስተኛ ስጦታዎች ውጪ ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት በልጁ ስም በስጦታ ለመስጠት አይችልም ።

## አንቀጽ ፪፻፹፯ የዋስትና ግዴታ መግባት የማይቻል ስለመሆኑ

ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት ለሌላ ሰው ዕዳ በዋስትና ሊያሲዝ አይችልም ።

## አንቀጽ ፪፻፹፰ ስለ ግልግል

ክርክር የሚደረግበት ጥቅም ከ፩ ሺህ ብር ያነሰ ካልሆነ ፣ ወይም አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ጥቅም በሚመለከት ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተቀር፡ ሞግዚቱ ጉዳዩን በግልግል ለመጨረስ አይችልም።

## አንቀጽ ፪፻፹፱ ሞግዚቱ አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ ጋር ስለማያደርጋቸው ውሎች

፩· ሞግዚቱ ፍርድ ቤት ካልፈቀደለት በስተቀር አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት ለመግዛት በኪራይ ለመጠቀም ወይም ሌላ ማናቸውንም ውል ከእርሱ ጋር ለመፈፀም አይችልም።

፪· እንዲሁም ሞግዚቱ በፍርድ ቤት ካልተፈቀደለት በስተቀር አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ላይ ማናቸውንም መብት ወይም ገንዘብ የሚጠይቅበትን መብት ለመቀበል አይችልም።

## አንቀጽ ፪፻፺ ስለብድር

ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተቀር ሞግዚቱ አካለመጠን ባልደረሰ ሰው ልጅ ስም የብድር ውል ለመዋዋል አይችልም።

## አንቀጽ ፪፻፺፩ አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ ጋር መመካከር ስለማስፈለጉ

፩· አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ዕድሜ ከ፲፬ ዓመት ያነሰ ካልሆነ በስተቀር፡ ሞግዚቱ የልጁ ዕድሜ በሚፈቅድለት መጠንና እርሱን የሚመለከቱ ከፍተኛ ጉዳዮች በተነሱ ጊዜ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ማማከር አለበት።

፪ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ፈቃዱን መስጠቱ ሞግዚቱን ከተጠያቂነት አያድነውም።

## አንቀጽ ፪፻፺፪ ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ እንዲሠራ ስለሚሰጠው ፈቃድ (፩) መሠረቱ

፩· አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ዕድሜና የገንዘብ አቅም መሠረት በማድረግ ፡ የዕለት ጉዳዮችን የሚመለከቱ ውሎችን ብቻ እንዲያደርግ ሞግዚቱ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል።

፪· ይኸው ፈቃድ በዝምታም ሊሰጥ ይችላል።

## አንቀጽ ፪፻፺፫ (፪) የዕለት ጉዳዮች

፩· ድርጊቱ እንዲፈፀም የፍርድ ቤት ፈቃድ የሚያስፈልገው እንደሆነ ፡ በምንም መንገድ የዕለት ጉዳይ ሊባል አይችልም።

፪· አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ከ፫፻ ብር በላይ ግዴታ እንዲገባ የሚያስገድደው ሲሆን ፡ ድርጊቱ የዕለት ጉዳይ ነው ሊባል አይችልም።

## አንቀጽ ፪፻፺፬ (፫) በሞግዚቱ ላይ ስለሚኖረው ውጤት

አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ በሞግዚቱ ፈቃድ ለሚገባቸው ግዴታዎች ሞግዚቱ ለሶስተኛ ወገኖች ዋስ ነው።

## አንቀጽ ፪፻፺፭ ኑዛዜ

፩· ሞግዚቱ አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ስም ኑዛዜ ሊያደርግ አይችልም።

፪· አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ፲፮ ዓመት ሳይሞላው ኑዛዜ ማድረግ አይችልም።

፫· አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ፲፮ ዓመት ሳይሞላው የሚያደርገው ኑዛዜ፣ ፲፮ ዓመት ከሞላው በኋላ ባይሰርዘውም ውጤት አይኖረውም።

## አንቀጽ ፪፻፺፮ ንብረት ለማስተዳደር ሞግዚት ስለሚያደርገው ወጪ

ሞግዚቱ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ ጥቅም ሲል ከግሉ የሚያወጣቸው ወጪዎች እንዲተኩለት መብት አለው።

## አንቀጽ ፪፻፺፯ አካለመጠን ስላልደረሰው ልጅ ሀብት አስተዳደር ሪፖርት ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ

፩· ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ሀብት አስተዳደር ሁኔታና ሂሳቡን የሚያመለክት ሪፖርት አዘጋጅቶ መያዝ አለበት።

፪· አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ወይም አካለመጠን የደረሱ ወንድሞቹና እህቶቹ በጋራ ወይም በተናጠል ጥያቄ ሲያቀርቡለት ፣ ሞግዚቱ የአስተዳደርና የሂሳብ ሪፖርቱን እንዲመለከቱት ያደርጋል።

## አንቀጽ ፪፻፺፰ ተፈጻሚነት

በዚህ ሕግ ከአንቀጽ ፪፻፹፩ እስከ ፪፻፺፯ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ለሞግዚትም ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

## ክፍል ፱

## አካለመጠን ያልደረሰን ልጅ ለመጠበቅ የተመለከቱትን ደንቦች መጣስ ስለሚያስከትለው ውጤት

## ንዑስ ክፍል ፩

## አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ሥራዎች

### አንቀጽ ፪፻፺፱ መሠረቱ

አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ከሥልጣኑ በላይ የሚፈጽማቸው ሕጋዊ ድርጊቶች ሁሉ ፈራሽ ይሆናሉ።

### አንቀጽ ፫፻ እንዲፈርስ ስለመጠየቅ

አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ የፈፀማቸው ሕጋዊ ድርጊቶች እንዲፈርሱ መጠየቅ የሚችሉት አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ፣ ወይም ወራሾቹ ወይም ወኪሎቹ ናቸው።

### አንቀጽ ፫፻፩ ስለተዋዋዩ ቅን ልቦና

፩· በዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፺፱ የተደነገገው ቢኖርም፣ ሌላው ተዋዋይ ወገን ከልጁ ጋር የተዋዋለው ይህንን እንዲያደርግ ፈቃድ አለው ብሎ በቅን ልቦና በማመን የሆነ እንደሆነ ውሉ የፀና ይሆናል።

፪· ሌላው ተዋዋይ በልጁ አላዋቂነት የተጠቀመ ከሆን ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ተፈጻሚነት አይኖረውም።

## አንቀጽ ፫፻፪ ስለሚመለስ ገንዘብ

፩· አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ የተከፈለ ገንዘብ ሊመለስ የሚችለው ውሉ እንዲፈርስ ክስ በቀረበበት ቀን በልጁ በተገኘው መጠን ብቻ ይሆናል።

፪· ከዚህ ሁኔታ ውጪ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ለመመለስ አይገደደም።

## አንቀጽ ፫፻፫ ከውል ውጭ ስለሚደርስ ኃላፊነትና ያለአግባብ ስለመበልጸግ (፩) መሠረቱ

አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ሕገወጥ በሆኑ ሥራዎች ያለአግባብ የበለፀገ ወይም በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፣ በፍትሐብሔር ሕግ ውስጥ ከውል ውጪ ስለሚደርስ ኃላፊነትና ያለአግባብ ስለመበልጸግ በተደነገገው መሠረት ተጠያቂ ይሆናል።

## አንቀጽ ፫፻፬ (፪) አካለመጠን ሳይደርስ ደርሻለሁ ማለት

፩· አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ አካለመጠን ሳይደርስ ደርሻለሁ ብሎ ቢናገርም እንኳን ይህን በመናገሩ ብቻ አካለመጠን ባለመድረሱ ምክንያት የሚጠቀምበትን መብት አያጣም።

፪· እንዲሁም አካለመጠን ደርሻለሁ ማለቱ፣ ከውል ውጪ የሆነ ኃላፊነትን የሚያመጣ ጥፋት ሆኖ አይቆጠርበትም።

### ንዑስ ክፍል ፪

### የሞግዚቱ ሕጋዊ ድርጊቶች

## አንቀጽ ፫፻፭ በደንብ ስለተፈፀሙ ድርጊቶች

፩· ሞግዚቱ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ የፈፀማቸው ሕጋዊ ድርጊቶች ሁሉ፣ ልጁ አካለመጠን በደረሰ ጊዜ እንደፈፀማቸው ተቆጥረው በኃላፊነት ያስጠይቁታል።

BACK



፪· ሞግዚቱ በኃላፊነት እጠየቅበታለሁ ሲል ግዴታ የገባበት ወይም በሕግ መሠረት ግዴታ የተጣለበት ካልሆነ በስተቀር ፡ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ ሲል ለፈፀማቸው ሕጋዊ ድርጊቶች ኃላፊ አይሆንም።

## አንቀጽ ፪፻፸፯ የሕግ ድንጋጌዎችን ስለመተላለፍ

የሕግ ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ሞግዚቱ ለሚፈፅማቸው ድርጊቶች፣ ወኪል የሆነ ሰው ከተሰጠው ሥልጣን በላይ በሚሠራበት ጊዜ አግባብነት ያላቸው የውክልና ሕግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## አንቀጽ ፪፻፸፰ ስለሦስተኛ ወገኖች

፩· ፍርድ ቤት ለሞግዚቱ የተሰጠውን መመሪያ ሶስተኛ ወገኖች ካላወቁ ወይም ማወቅ የሚገባቸው ካልሆነ በስተቀር ሞግዚቱ መመሪያውን መተላለፉ፣ በሶስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሊሆን አይችልም።

፪· አካለመጠን ላልደረሰ ልጅ ንብረቱን የሰጠ፣ የተናዘዘ ወይም የተወ ሰው ለሞግዚቱ መመሪያ በሰጠ ጊዜም የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል።

## አንቀጽ ፪፻፸፱ ስለምትክ ሞግዚት

በዚህ ንዑስ ክፍል የተመለከቱት ድንጋጌዎች በምትክ ሞግዚትም ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## ንዑስ ክፍል ፫

## በኃላፊነት ሊያስጠይቁ ስለሚችሉ ድርጊቶች

## አንቀጽ ፪፻፹ ስለሞግዚት

፩· ሞግዚቱ በፈፀመው የንብረት አስተዳደር ጉድለት ምክንያት ወይም መመሪያ ባለማክበሩ ወይም የእርሱ ጥቅም አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ ጥቅም ጋር የሚጋጭ ሆኖ እያለ ድርጊቱን በመፈፀሙ

አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ሁሉ በኃላፊነት ይጠየቃል።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ድንጋጌ በምትክ ሞግዚትም ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## ክፍል ፫
## አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ችሎታ ማጣት ስለመቅረት

### አንቀጽ ፫፻፲ ችሎታ ማጣት ስለሚቀርባቸው ምክንያቶች

አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ችሎታ የለውም መባሉ የሚቀረው፡

ሀ) አካለመጠን ሲደርስ፡ ወይም
ለ) ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ይውጣ ሲባል ፡ ነው።

## ንዑስ ክፍል ፩
## ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ስለመውጣት

### አንቀጽ ፫፻፲፩ ጋብቻ

አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ በዚህ ሕግ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተመለከተው መሠረት ጋብቻ የፈፀመ እንደሆነ በጋብቻው ምክንያት ብቻ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ይወጣል።

### አንቀጽ ፫፻፲፪ በልዩ ሁኔታ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ስለመውጣት

፩. አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ፲፭ ዓመት ሲሞላው አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ፡ ወይም ያገባኛል የሚል ሌላ ሰው ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ እንዲወጣ መጠየቅ ይችላል።

፪. ፍርድ ቤት ጥያቄው ሲቀርብለት፡ የልጁን ሁኔታና ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ እንዲወጣ የተጠየቀበትን ምክንያት ተመልክቶ፡ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ መሆኑ ለልጁ የሚጠቅም ሆኖ ካገኘው ጥያቄውን ተቀብሎ ሊፈቅድ ይችላል።

BACK



**አንቀጽ ፫፻፲፫ ውጤቶች**

ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ የወጣ ልጅ በሕግ አካለመጠን እንደደረሰ ሆኖ ይቆጠራል።

**አንቀጽ ፫፻፲፬ የማይሻር ስለመሆኑ**

፩· አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ እንዲሆን የተሰጠ ፈቃድ ሊሻር አይችልም።

፪· በጋብቻ ምክንያት የተገኘው ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ የመሆን ሁኔታ፣ ጋብቻው ቢፈርስም እንኳን ውጤቱ እንደተጠበቀ ይቀራል።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም፣ ጋብቻው የፈረሰው ለጋብቻ የተፈቀደው ሕጋዊ ዕድሜ ባለመጠበቁ ምክንያት የሆነ እንደሆነ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ መውጣቱን በተመለከተ ፍርድ ቤቱ ተገቢ መስሎ የታየውን ሊወስን ይችላል።

**ንዑስ ክፍል ፪**

**የሞግዚትነት ሥራ ሂሳቦችን ስለማስታወቅ**

**አንቀጽ ፫፻፲፭ መሠረቱ**

፩· ሞግዚቱ የሞግዚትነት ሥራው ሲያበቃ፣ ሞግዚት ሆኖ ለአስተዳደረው ሰው ወይም ለወራሾቹ ያስተዳደረበትን ሂሣብ ማቅረብ አለበት።

፪· እንዲሁም በሞግዚትነት ያስተዳደረውን ሰው ንብረት ሁሉ ማስረከብ፣ የመብቶቹን ሁኔታና የሚገደድባቸው ዕዳዎች ካሉም ማስታወቅ አለበት።

BACK



## አንቀጽ ፫፻፲፮ የንብረቶች በመዝገብ አለመግባት

፩· ሞግዚቱ የሞግዚትነት ሥራውን በያዘበት ጊዜ ወይም አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ በውርስ ሀብት ሲሰጠው የንብረቶቹን ዝርዝር በመዝገብ ከመያዝ ቸል ያለ እንደሆነ፣ የልጁን ንብረት፣ በውርስ ወይም በስጦታ ያገኘውን ሀብት በማናቸውም ሁኔታ ለማስረዳት ይቻላል።

፪· ሌላ ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር፣ ምስክሮች በሚሰጡት ቃል አንድ ንብረት አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረት እንደሆነ ይቆጠራል።

## አንቀጽ ፫፻፲፯ ሂሣቦችን ስለማፅደቅ

፩· ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ የወጣው ልጅ የሞግዚቱን ሥራ ሂሣቦች ያጸደቀ እንደሆነና ዕድሜው ፲፰ ዓመት ያልሞላው ከሆነ ሂሣቦቹን ካጸደቀ በኋላ እስከ አንድ ዓመት ድረስ አጽድቆት የነበረውን ሂሣብ ራሱ ሊያፈርሰው ይችላል።

፪· ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ የወጣው ልጅ ሂሣብ እንዳያቀርብ ለሞግዚቱ ፈቃድ ሰጥቶ የነበረ ቢሆንም ከዚህ በላይ ያለው ድንጋጌ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

፫· አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ አካለመጠን የደረሱ ሲወርሱት፣ እነዚህ ወራሾች የልጁ ሞግዚት ያደረገውን ሂሣብ ያጸደቁት ወይም ሞግዚቱን ሂሣብ ከማቅረብ ነፃ አውጥተውት እንደሆነ ከዚህ በላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ጠቅሰው ለመከራከር አይችሉም።

## አንቀጽ ፫፻፲፰ ስለ ይርጋ

፩· አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ፣ ወኪሎቹ ወይም ወራሾቹ በሞግዚትነት ሥራ ምክንያት በሞግዚቱ ላይ ስለኃላፊነት የሚያቀርቧቸው ማናቸውም ክሶች፣ ሞግዚቱ የሞግዚትነት

BACK



ሥራውን ከተወበተ ጊዜ ጀምሮ እስከ አምስት ዓመት ሳያቀርቡ የቀሩ እንደሆነ በይርጋ ይታገዳሉ።

፪· ሆኖም አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረቶቹ እንዲመለሱለት ለመጠየቅ ክስ የማቅረብ መብቱ፣ ከዚህ በላይ የተመለከተው ጊዜ ካለፈ በኋላም ቢሆን አይከለከልም።

## ምዕራፍ አሥራ ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ ፫፻፲፱ ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

፩· በ፲፱፻፶፪ ዓ·ም· በወጣው የፍትሐብሔር ሕግ ፤

ሀ) "ስለ ሰዎች" ከሚለው አንደኛ መጽሐፍ ውስጥ ከአንቀጽ ፩፻፺፰—፫፻፴፰፣

ለ) "ስለ ቤተ ዘመድና ስለውርስ" ከሚለው ሁለተኛ መጽሐፍ ውስጥ ከአንቀጽ ፭፻፶—፰፻፳፭፣

ያሉ ድንጋጌዎች፣ ይህ ሕግ ተግባራዊ በሚሆንባቸው መስተዳድሮች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

፪· ይህን አዋጅ የሚቃረኑ ሕጎች፣ መመሪያዎች፣ ውሳኔዎችና የአሠራር ልምዶች ይህን አዋጅ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም።

### አንቀጽ ፫፻፳ በቀድሞ ሕጎች መሠረት ተገኝተው ስለነበሩ መብቶች

፩· ግልጽ የሆነ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር፣ ይህ ሕግ ከመጽናቱ በፊት የነበሩ ሕጋዊ ሁኔታዎችን ለማስገኘት አዲሱ ሕግ የሚጠይቃቸው መመዘኛዎች ከድሮው የተለዩ ቢሆኑም እንኳን፣ በቀድሞው ሕግ መሠረት ተገኝተው የነበሩት ሕጋዊ ሁኔታዎች ፀንተው ይቀጥላሉ።

፪· ግልጽ የሆነ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር፣ ይህ ሕግ ከመጽናቱ በፊት፣ በቀድሞው ሕግ መሠረት ተገኝተው የነበሩት

ሕጋዊ ሁኔታዎች ያስገኟቸውን ውጤቶች ይህ ሕግ አይለውጣ ቸውም።

## አንቀጽ ፫፻፴፩ ስለምዝገባ

፩· የፌዴራሉ መንግሥት ይህ ሕግ በሥራ ላይ በዋለ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ሕጉ ተፈፃሚ ለሚሆንባቸው መስተዳድሮች የሚያገ ለግል የምዝገባ ሕግ ያወጣል፤ አስፈላጊ ተቋሞችንም ያደራጃል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የክብር መዝገብ ሹም ጽሕፈት ቤት ተቋቁሞ ሥራውን እስኪጀምር ድረስ ሕጉ ተፈፃሚ በሚሆንባቸው መስተዳድሮች አግባብ ባለው አካል የተሰጡ ወይም የሚሰጡ የልደት፣ የጋብቻና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የምስክር ወረቀቶች በክብር መዝገብ ሹም እንደተሰጡ ሰነዶች ተቆጥረው ሕጋዊነት ይኖራቸዋል።

## አንቀጽ ፫፻፴፪ በእንጥልጥል ስላሉ የቤተሰብ ጉዳይ ክርክሮች

፩· ይህ ሕግ ከመጽናቱ በፊት በፍርድ ቤት የተያዙ የቤተሰብ ጉዳይ ክርክሮች በዚህ ሕግ መሠረት ፍፃሜ ያገኛሉ።

፪· ይህ ሕግ ከመጽናቱ በፊት በቀድሞው ሕግ መሠረት በቤተ ዘመድ ሽምግልና ጉባኤ የተያዙ የፍቺ ክርክሮች በሙሉ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ሥልጣን ወዳላቸው ፍርድ ቤቶች ይተላ ለፋሉ።

፫· ፍርድ ቤቶችም እነዚህን ጉዳዮች ተረክበው በዚህ ሕግ ድንጋ ጌዎች መሠረት ውሳኔ ይሰጣሉ።

## አንቀጽ ፫፻፴፫ ደንብ የማውጣት ስልጣን

፩· የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ ሕግ አፈጻጸም ደንብ ማውጣት ይችላል።

፪· ይህ ሕግ ተፈፃሚ የሚሆንባቸው መስተዳድሮችም ለሕጉ አፈፃፀም የሚረዳ መመሪያ እና የአሠራር ሥነ ሥርዓት ደንብ ማውጣት ይችላሉ።